# ጓደኝነት

1. መጥፎ ጓደኝነት መልካሙን ዐመል ያጠፋዋል::

1ኛ ቆሮ. 15:33:: አትሳቱ፤ «መጥፎ ጓደኝነት መልካሙን ጠባይ ያበላሻል::»

2. ጓደኞቻችን መጥፎም ሆነ ጥሩ ተጽዕኖ ያሳድሩብናል::

ምሳ. 13:20:: «ከጠቢብ ጋር የሚሄድ ጠቢብ ይሆናል፤ የተላሎች ባልንጀራ ግን ጉዳት ያገኘዋል::»

3. እውነተኛ ጓደኛ በአስፈላጊው ጊዜ መልካም ምክርን በመስጠት ይደግፈናል::

ምሳ. 28:23:: «ሽንጋይ አንደበት ካለው ይልቅ፣ ሰውን የሚገሥጽ ውሎ አድሮ ይወደዳል::»

4. ከሞኝ ሰው ራቅ::

ምሳ. 14:7:: «ከተላላ ሰው ራቅ፤ ከከንፈሮቹ ዕውቀት አታገኝምና::»

5. ከቁጡ ሰው ጋር ጓደኛ አትሁን::

ምሳ. 22:24:: «ከግልፍተኛ ጋር ወዳጅ አትሁን፤ በቀላሉ ቱግ ከሚል ሰው ጋር አትወዳጅ::»

6. እውነተኛ ጓደኛ (ወዳጅ) አንተን ለመጥቀም ሲል አንድ ጊዜ የሚጐዳህ ነው::

ምሳ. 25:11-12:: «ባግባቡ የተነገረ ቃል፣ በብር መደብ ላይ እንደ ተቀረጸ የወርቅ እንኮይ ነው:: የጠቢብ ሰው ዘለፋ ለሚሰማ ጆሮ፣ እንደ ወርቅ ጕትቻ ወይም እንደ ጥሩ የወርቅ ጌጥ ነው::»

ምሳ. 27:6:: «ከጠላት ደጋግሞ መሳም ይልቅ፣ የወዳጅ ማቍሰል ይታመናል::»

7. መንፈሳዊ ጓደኛ ጥሩ ረዳት ሊሆን ይችላል::

ምሳ. 27:9:: «ሽቱና ዕጣን ልብን ደስ ያሰኛሉ፤ የወዳጅ ማስደሰትም ከቅን ምክሩ ይመነጫል::»



ምሳ. 27:17:: «ብረት ብረትን እንደሚስል፣ ሰውም ሌላውን ሰው እንደዚሁ ይስለዋል::»

8. ዮናታንና ዳዊት ሊጠቀስ የሚችል ግሩም ጓደኝነት ነበራቸው::

1ኛ ሳሙ. 20::

1ኛ ሳሙ 20:17:: «ዮናታን ከፍቅሩ የተነሣ ዳዊት እንደ ገና እንዲምልለት አደረገ፤ ዳዊትን የሚወደውም እንደ ራሱ አድርጎ ነበርና::»

1ኛ ሳሙ. 23:16:: «የሳኦል ልጅ ዮናታንም ዳዊት ወዳለበት ወደ ሖሬብ ሄዶ፣ በእግዚአብሔር ስም አበረታታው፤»

9. ከዓለም ጋር መወዳጀት ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት ነው::

ያዕ. 4:4:: «አመንዝሮች ሆይ፤ ከዓለም ጋር ወዳጅ መሆን የእግዚአብሔር ጠላት መሆን እንደ ሆነ አታውቁምን? ስለዚህ የዓለም ወዳጅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል::

1ኛ ዮሐ. 2:15-17:: «ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማናቸውንም ነገር አትውደዱ፤ ማንም ዓለምን ቢወድ፣ የአብ ፍቅር በእርሱ ዘንድ የለም፤ ምክንያቱም በዓለም ያለው ሁሉ፡- የሥጋ ምኞት፣ የዐይን አምሮትና የኑሮ ትምክሕት ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ አይደለም:: ዓለምና ምኞቱ ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም ግን ለዘላለም ይኖራል::

# መስጠት

## 1. ኢየሱስ የመበለቲቱን ስጦታ ከልቡ አረጋገጠ።

ሉቃ. 21:1-4። «ኢየሱስ ቀና ብሎ ሲመለከት ሀብታሞች በቤተ መቅደሱ መባ መሰብሰቢያ ውስጥ መባቸውን ሲጨምሩ አየ። ደግሞም አንዲት ድኻ መበለት ሁለት ትናንሽ የናስ ሳንቲሞች በዚያ ስትጨምር ተመለከተ። እንዲህም አለ፤ «እውነት እላችኋለሁ፤ ከሁሉም ይልቅ ይህች ድኻ መበለት የበለጠ ሰጥታለች፤ እነዚህ ሰዎች የሰጡት ከትርፋቸው ላይ ሲሆን፣ እርሷ ግን የሰጠችው በድኻ አቅሟ ያላትን መተዳደሪያ በሙሉ ነው።»

## 2. ጌታ በልግስናና በደስታ እንድንሰጥ ይፈልጋል።

2ኛ ቆሮ. 8:1-9። *(የመቄዶንያ ክርስቲያኖች ምሳሌ)*

2ኛ ቆሮ. 8:1-5። «ወንድሞች ሆይ፤ እግዚአብሔር በመቄዶንያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት የሰጠውን ጸጋ እንድታውቁ እንፈልጋለን። የደረሰባቸው መከራ ጽኑ ቢሆንም ደስታቸው ግን የላቀ ነበር፤ ድኽነታቸው ብርቱ ቢሆንም ልግስናቸው ግን የበዛ ነበር። እንደ ዐቅማቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከዐቅማቸው በላይ በፈቃዳቸው እንደ ሰጡ እመሰክርላቸዋለሁ። እነርሱም ቅዱሳንን ለመርዳት በሚደረገው አገልግሎት ለመሳተፍ ዕድል ያገኙ ዘንድ አጥብቀው ይለምኑት ነበር። እኛ ከጠበቅነው በላይ፣ በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ፤ ቀጥለውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለእኛ ሰጡ።»

2ኛ ቆሮ. 8:11-12። «አሁንም የጀመራችሁትን ተግባር በዐቅማችሁ መጠን ከፍጻሜ አድርሱት፤ ይህም ለመስጠት የነበራችሁ በጎ ፈቃድ እውን እንዲሆን ነው። ለመስጠት በጎ ፈቃድ ካለን ስጦታው ተቀባይነት የሚያገኘው ባለን መጠን ስንሰጥ እንጂ፣ በሌለን መጠን ለመስጠት ስንሞክር አይደለም።

2ኛ ቆሮ. 9:6-7። «ይህን አስታውሱ፤ ጥቂት የዘራ ጥቂት ያጭዳል፤ ብዙ የዘራ ብዙ ያጭዳል። እያንዳንዱ ሰው በቅሬታ ወይም በግዴታ ሳይሆን፣ በልቡ ያሰበውን ያህል ይስጥ፤ ምክንያቱም



እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ሰው ይወዳል።»

## 3. ባለጠጎች የሆኑ እንደ ብልጥግናቸው መጠን መስጠት አለባቸው።

1ኛ ጢሞ. 6:17። «በዚህ ዓለም ባለጠጎች የሆኑት እንዳይታበዩ፣ ደስም እንዲለን ሁሉን ነገር አትረፍርፎ በሚሰጠን በእግዚአብሔር እንጂ አስተማማኝነት በሌለው በሀብት ላይ ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው። መልካም እንዲሠሩ፣ ቸሮችና ለማካፈል ፈቃደኞች የሆኑ እንዲሆኑ እዘዛቸው። በዚህ ዐይነት እውነተኛ የሆነውን ሕይወት ያገኙ ዘንድ፣ ለሚመጣው ዘመን ጽኑ መሠረት የሚሆን ሀብት ለራሳቸው ያከማቻሉ።»

## 4. እያንዳንዱ ክርስቲያን ጌታ በባረከው መጠን መስጠት አለበት።

1ኛ ቆሮ. 16:1-2። «አሁን ደግሞ ለቅዱሳን ስለሚደረገው ገንዘብ ማሰባሰብ ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት በሰጠሁት ትእዛዝ መሠረት አድርጉ። ገንዘብ ማሰባሰብ የሚደረገው እኔ በምመጣበት ጊዜ እንዳይሆን፣ ከእናንተ እያንዳንዱ እንደ ገቢው መጠን በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን እየለየ ያስቀምጥ።»

## 5. እግዚአብሔርን በአሥራትና በመባ አትስረቁት።

ሚል. 3:7-10። «ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ከትእዛዛቴ ፈቀቅ ብላችኋል፤ አልጠበቃችኋቸውምም፤ ወደ እኔ ተመለሱ፤ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ። ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት። «እናንተ ግን፣ የምንመለሰው እንዴት ነው ትላላችሁ?» ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን?» እናንተ ግን ትሰርቁኛላችሁ። «እናንተ ግን እንዴት እንሰርቅሃለን? ትላላችሁ። «አሥራትና መባ ትሰርቁኛላችሁ፤ እናንተም፣ መላው ሕዝባችሁም ስለምትሰርቁኝ የተረገማችሁ ናችሁ። በቤቴ መብል እንዲኖር፣ እኔንም በዚህ እንድትፈትኑኝ ዐሥራቱን ሁሉ ወደ ጐተራ አስገቡ፤» ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት፤ «የሰማይን መስኮት የማልከፍትላችሁ፣ የተትረፈረፈ በረከትንም ማስቀመጫ እስከታጡ ድረስ የማላፈስላችሁ ከሆነ ተመልከቱ።»

## 6. አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ።

ማቴ. 6:33:: «ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል::»

7. በሰዎች ለመታየት ብላችሁ አትስጡ::

ማቴ. 6:1-4:: «ሰዎች እንዲያዩላችሁ፣ መልካም ሥራችሁን በፊታቸው ከማድረግ ተጠንቀቁ፤ እንዲህ ካደረጋችሁ ከሰማዩ አባታችሁ ዋጋ አታገኙም:: በሰዎች ዘንድ ለመከበር ብለው በየጎዳናውና በየምኵራቡ ጥሩምባ እንደሚያስነፉ ግብዞች፣ እናንተም ለድኾች ምጽዋት በምትሰጡበት ጊዜ ይታይልኝ ብላችሁ አታድርጉ፤ እውነት እላችኋለሁ እንዲህ የሚያደርጉ ዋጋቸውን በሙሉ ተቀብለዋል:: እናንተ ግን ለድኾች ስትሰጡ ቀኝ እጃችሁ የሚያደርገውን ግራ እጃችሁ አይወቅ፤ ምጽዋታችሁ በስውር ይሁን፤ በስውር የተደረገውን የሚያይ አባታችሁም ዋጋችሁን ይከፍላችኋል::»

8. እግዚአብሔር ምሕረት የምናደርግና ለድሆች የምንሰጥ እንድንሆን ይጠብቅብናል::

ምሳ. 14:21:: «ጎረቤቱን የሚንቅ ኀጢአት ይሠራል፤ ለተቸገሩት የሚራራ ግን ቡሩክ ነው::»

ምሳ. 19:17:: ለድኻ የሚራራ ለእግዚአብሔር ያበደራል፤ ስላደረገውም ተግባር ዋጋ ይከፍለዋል::

ምሳ. 22:9:: «ቸር ሰው ራሱ ይባረካል፤ ምግቡን ከድኾች ጋር ይካፈላልና::»

ማቴ. 5:7:: «ምሕረት የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው፤ ምሕረትን ያገኛሉና::»

ገላ. 6:9-10:: «በጎ ነገር ከማድረግ አንታክት፤ ተስፋ ካልቈረጥን ጊዜው ሲደርስ መከሩን እናጭዳለን:: ስለዚህም ዕድሉ ካለን ለሰው ሁሉ፣ በተለይም ለእምነት ቤተ ሰቦች መልካም እናድርግ::»

9. ለእግዚአብሔር ልጆች መስጠት ለክርስቶስ መስጠት ነው::

ማቴ. 24:34-46::

ማቴ. 25: 35፣40:: «ምክንያቱም ተርቤ አብልታችሁኛል፤



ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል፤ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛል. . .» ንጉሡም መልሶ <እውነት እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት፣ ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው> ይላቸዋል::

10. ምሕረት የምታደርጉና ለጠላቶቻችሁ እንኳ መልካም የምታደርጉ ሁኑ:: የእግዚአብሔርን አርአያነት (ምሳሌ) ተከተሉ::

ሉቃ. 6:27-36::

ሉቃ. 6:27-28 «ነገር ግን ለእናንተ ለምትሰሙ እላችኋለሁ፤ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ፣ የሚረግሟችሁን መርቁ፤ ለሚበድሏችሁም ጸልዩ::»

11. ተራ ንግግር በቂ አይደለም::

1ኛ ዮሐ. 3:16-18:: «ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ስለ እኛ አሳልፎ ስለ ሰጠ፣ ፍቅር ምን እንደ ሆነ በዚህ እናውቃለን፤ እኛም ሕይወታችንን ስለ ወንድሞቻችን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባናል:: ማንም ሀብት እያለው፣ ወንድሙ ሲቸገር አይቶ ባይራራለት፣ የእግዚአብሔር ፍቅር እንዴት በእርሱ ይኖራል? ልጆች ሆይ፤ በተግባርና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት ብቻ አንዋደድ::»

12. እንደ እስራኤል መሪ ንጉሥ ዳዊትና ለእግዚአብሔር ቤት ግንባታ በፈቃዳቸውና በነጻነት እንደሰጡ ሌሎች ሰዎች ዓይነት ጥሩ የመስጠት ምሳሌዎች እናያለን::

1ኛ ዜና 29:1-9::

1ኛ ዜና 29:3:: ከዚህም በቀር ለአምላኬ ቤት ካለኝ ፍቅር የተነሣ ለዚህ ለተቀደሰ ቤት ከዚህ በፊት ከሰጠሁት በተጨማሪ ለዚሁ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የግል ሀብቴ የሆነውን ወርቅና ብር እሰጣለሁ::

1ኛ ዜና 29:6:: «ከዚያም የቤተ ሰቡ መሪዎች፣ የነገዱ የእስራኤል ሹማምንት፣ የሻለቆችና የመቶ አለቆች እንዲሁም በንጉሡ ሥራ ላይ የተመደቡ ሹማምንት በፈቃዳቸው ሰጡ::

1ኛ ዜና 29:9:: «ስጦታው በገዛ ፈቃድና በፍጹም ልብ የቀረበ በመሆኑ፣ አለቆቹ ስላደረጉት የበጎ ፈቃድ ስጦታ ሕዝቡ ደስ አለው፤ ንጉሥ ዳዊትም እንደዚሁ እጅግ ደስ አለው።»

13. በልግስና የሚሰጥ ይባረካል፣ ነገር ግን ንፉግ ሰው ይጐዳል።

ምሳ. 11:24-25:: «አንዱ በለጋስነት ይሰጣል፤ ሆኖም ይበልጥ ያገኛል፤ ሌላው ያለመጠን ይሰስታል፤ ግን ይደኸያል። ለጋስ ይበለጽጋል፤ ሌሎችን የሚያረካም ራሱ ይረካል።»

14. ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ የተባረከ ነው።

ሐዋ. 20:35:: «በጉልበታችን ደክመን ችግረኞችን መርዳት እንዳለብን ባደረግሁት ሁሉ አሳይቻችኋለሁ፤ <ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው> ያለውን የጌታ የኢየሱስን ቃል እናስታውስ።»

15. ማስቀደም የሚገባችሁን አስቀድሙ። የምትፈልጉትን እስከምታገኙ ደረስ መስጠትን አታቁሙ።

ሐጌ. 1::

ሐጌ. 1:2-4:: «እግዚአብሔር ጸባኦት እንዲህ ይላል፤ «ይህ ሕዝብ፣ <የእግዚአብሔር ቤት የሚሠራበት ጊዜ ገና ነው> ይላል። የእግዚአብሔርም ቃል በነቢዩ በሐጌ በኩል እንዲህ ሲል መጣ፤ «ይህ ቤት ፈርሶ ሳለ፣ እናንተ ራሳችሁ በተዋቡ ቤቶቻችሁ ውስጥ ለመኖር ጊዜው ነውን?»



# ግብረ ሰዶማዊነት

ግብረ ሰዶማዊያንን ለመርዳት፣ መለወጥን በገጽ 142፤ የኃጢአቶች ይቅርታን በገጽ 90፤ ሰላምን በገጽ 148፤ ኃጢአትን ማሸነፍን በገጽ 142፤ ንስሐን በገጽ 186፣ እንዲሁም ዘማዊነትን በገጽ 214 ተመልከቱ።

1. እግዚአብሔር ቁርጥ ባለ መልኩ የግብረ ሰዶማዊነትን ድርጊት ይቃወማል።

ዘሌ. 18:22:: «ከሴት ጋር እንደሚደረገው ሁሉ ከወንድ ጋር አትተኛ፤ ይህ አስጸያፊ ነው።»

2. እግዚአብሔር ሰዶምና ገሞራን ስለ ግብረ ሰዶማዊ ተግባራቸው ቀጣቸው። ግብረ ሰዶማዊነት ኃጢአት ነው።

ዘፍ. 18:20-21:: «ደግሞም እግዚአብሔር (ያህዌ) እንዲህ አለ፤ «በሰዶምና በገሞራ ላይ የሚሰማው ጩኸት እጅግ በዝቶአል፤ ኀጢአታቸውም እጅግ ከፍቶአል፤ አድራጎታቸው እኔ ዘንድ እንደ ደረሰው ጩኸት መሆኑን ለማየት ወደዚያው እወርዳለሁ፤ እንደዚያ ካልሆነም አውቃለሁ።»

3. ሰዶምና ገሞራ ንስሐ ባለመግባታቸው ምክንያት ጠፉ።

ዘፍ. 19::

ዘፍ.19:4-5:: «ከመተኛታቸውም በፊት፣ የሰዶም ከተማ ነዋሪዎች የሆኑ ወንድ ወጣቶችና ሽማግሌዎች ከያካባቢው ወጥተው ቤቱን ከበቡት። ሎጥንም ጠርተው፣ «በዚህች ምሽት ወደ ቤትህ የገቡ ሰዎች የት አሉ? ሩካቤ ሥጋ እንድንፈጽምባቸው ወደ ውጭ አውጣልን» አሉት።»

ዘፍ. 19:24-25:: «ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) በሰዶምና በገሞራ ላይ ከሰማይ ከእግዚአብሔር (ያህዌ) ዘንድ የሚያቃጥል ዲንና እሳት አዘነበባቸው። እነዚያንም ከተሞችና ረባዳውን ምድር በሙሉ፣ በከተሞቹም የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ፣ የምድሩን ቡቃያ ሳይቀር ገለባበጠው።»

4. የሰዶምና የገሞራ ምሳሌ በሁሉም ዘመናት ለሚኖሩ ሰዎች እንደ

**ማስጠንቀቂያ ሆኖ በምሳሌነት ቀርቧል። እግዚአብሔር ግብረ ሰዶማውያንን ለሠሩት ኃጢአት ይጠይቃቸዋል።**

2ኛ ጴጥ. 2:4-10።

2ኛ ጴጥ. 2:6-10። «ደግሞም ኀጢአት ለሚያደርጉ ሁሉ ምሳሌ እንዲሆኑ የሰዶምንና የገሞራን ከተሞች ዐመድ እስኪሆኑ ድረስ አቃጥሎ ከፈረደባቸው፣ ጻድቅ የሆነውንና በዐመፀኞች ሴሰኛ ድርጊት እየተሠቃቀ የኖረውን ሎጥን ካዳነ፣ ያ ጻድቅ ሰው በእነርሱ መካከል ሲኖር በሚያየውና በሚሰማው ነገር ነፍሱ ዕለት ዕለት በዐመፀኛ ድርጊታቸው ብትጨነቅም፣ ጌታ፣ በእውነት እያመለኩት የሚኖሩትን ከፈተና እንዴት እንደሚያድናቸውና ዐመፀኞችን እየቀጣ ለፍርድ ቀን እንዴት ጠብቆ እንደሚያቈያቸው ያውቃል። በተለይም በርኩስ ምኞት የሥጋ ፍላጐታቸውን የሚከተሉትንና ሥልጣንን የሚንቁትን ለፍርድ ጠብቆ ያቈያቸዋል። እነዚህ ሰዎች ደፋሮችና እብሪተኞች ስለ ሆኑ ሰማያውያንን ፍጡራን ሲሳደቡ አይፈሩም።»

ይሁዳ 6-7። «የሥልጣን ስፍራቸውን ያልጠበቁትን ነገር ግን መኖሪያቸውን የተዉትን መላእክት በዘላለም እስራት እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ በጨለማ ጠብቆአቸዋል። እንዲሁም ሰዶምና ገሞራ፣ በዙሪያቸውም ያሉ ከተሞች ለሴሰኛነትና ከተፈጥሮ ሥርዐት ውጭ ለሆነ ሩካቤ ሥጋ ራሳቸውን አሳልፈው ሰጡ፤ እነርሱም በዘላለም እሳት በመቀጣት ለሚሠቃዩት ምሳሌ ሆነዋል።

5. **በዐመፀኞችና በክፉ ሰዎች ሁሉ ላይ ግብረ ሰዶማውያንንም ጨምሮ የእግዚአብሔር ቁጣ ይገለጣል።**

ሮሜ 1. 18-32።

6. **ጳውሎስ፣ ግብረ ሰዶማዊነትን የእግዚአብሔርን ስጦታ በክፋት እንደ ማጣመም አድርጎ ይወስደዋል።**

ሮሜ. 1:26-27። «በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር አሳፋሪ ለሆነ ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም እንኳ ለባሕርያቸው የሚገባውን ግንኙነት ባሕርያቸው ላልሆነው ግንኙነት ለወጡ። እንደዚሁም ወንዶች ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት



ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወት ተቃጠሉ፤ ከወንዶች ጋር ነውር ፈጸሙ፤ ለክፉ አድራጎታቸውም የሚገባቸውን ቅጣት በገዛ ራሳቸው ላይ አመጡ።»

7. **ግብረ ሰዶማዊያንን ጨምሮ ርኩሳን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገቡም።**

1ኛ ቆሮ. 6:9-10። «ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እደማይወርሱ አታውቁምን? በዚህ ነገር አትታለሉ፤ ሴሰኞች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ አመንዝሮች፣ ወንደቃዎች፣ ግብረሰዶማውያን፣ ወይም ሌቦች ስግብግቦች፣ ሰካራሞች፣ ተሳዳቢዎችና ቀማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።»

8. **ለግብረ ሰዶማውያን ተስፋ አለ። በዚህ ኃጢአት ውስጥ ያሉትን ሰዎች እግዚአብሔር ይቅር ይላል፣ ያነፃልም።**

1ኛ ቆሮ. 6:11። «ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና፣ በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል።»

# ተስፋ

በተጨማሪ መታመን፣ እግዚአብሔርን ማመን የሚለውን በገጽ 224 ተመልከቱ::

1. እግዚአብሔር ለችግሮቻችን መፍትሔዎች አሉት::

1ኛ ቆሮ. 10:13:: «በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገሥ እንድትችሉ፣ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል::»

2. የእግዚአብሔር ጸጋ ለየትኛው ፍላጐት በቂ ነው::

2ኛ ቆሮ. 9:8:: «ሁልጊዜ በሁሉ ነገር የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ ሁሉ እንድትተርፉ፣ እግዚአብሔር ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል::»

3. እግዚአብሔር ከምንጠይቀውና ከምናስበው በላይ ሊያደርግ ይችላል::

ኤፌ. 3:20:: «እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው እንደ ኃይሉ መጠን፣ ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ በላይ እጅግ አብልጦ ማድረግ ለሚቻለው፣» [እግዚአብሔር] ::

4. እግዚአብሔር ሁልጊዜ ታማኝ ነው::

ሰቆ. 3:32:: «መከራን ቢያመጣ እንኳ ይራራል፤ ታላቅ ፍቅሩ አይለወጥምና»

5. ተስፋ የነፋስ መልሕቅ ነው::

ዕብ. 6:19-20:: «እኛም የነፍስ መልሕቅ የሆነ ጽኑና አስተማማኝ ተስፋ አለን፤ ይህም ተስፋ ከመጋረጃው በስተጀርባ ወዳለው ውስጠኛ መቅደስ ይገባል:: ይህም ስፍራ ኢየሱስ ስለ እኛ ቀድሞ የገባበት ነው:: እርሱም እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት ሆኖአል::»

6. ተስፋችሁን በእግዚአብሔር ላይ አድርጉ::



መዝ. 42::

መዝ. 42:5:: «ነፍሴ ሆይ፤ ለምን ትተክዢያለሽ? ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ? ተስፋሽን በአምላክ ላይ አድርጊ፤

7. ተስፋችሁን በታማኙና በሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር ላይ አድርጉ::

መዝ. 146:3-10::

መዝ. 146:5-6:: «ረዳቱ የያዕቆብ አምላክ የሆነ፣ ተስፋውንም በአምላኩ በእግዚአብሔር ላይ የጣለ ሰው ምስጉን ነው፤ እርሱ ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንም፣ በእነዚህም ውስጥ ያለውን ሁሉ የፈጠረ፣ ታማኝነቱንም ለዘላለም የሚጠብቅ ነው::»

8. ተስፋ ጽናትን ይፈጥራል::

1ኛ ተሰ. 1:3:: «ከእምነት የሆነውን ሥራችሁን፣ ከፍቅር የመነጨውን ድካማችሁንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ባላችሁ ተስፋ የተገኘውን ጽናታችሁን በአምላካችንና በአባታችን ፊት ዘወትር እናስባለን::»

9. አማኞች በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ምክንያት ሕያው ተስፋ አላቸው::

1ኛ ጴጥ. 1:3:: «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ይባረክ፤ እርሱ ከታላቅ ምሕረቱ የተነሣ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣት ምክንያት ለሕያው ተስፋ በሚሆን አዲስ ልደት፣ እንዲሁም በሰማይ ለማይጠፋ፣ ለማይበላሽና ለማይለወጥ ርስት እንደገና ወለደን::»

10. በተስፋ አምላክ በእግዚአብሔር መታመን ገና የበለጠ ደስታ፣ ሰላምና ተስፋን ያመጣል::

ሮሜ 15:13:: «በእርሱ በመታመናችሁ የተስፋ አምላክ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ፤ ይኸውም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተስፋ ተትረፍርፎ እንዲፈስላችሁ ነው::»

# ኢየሱስን መምሰል

በተጨማሪ ሌሎችን መውደድና ማገልገል የሚለውን በገጽ 118 ላይ ተመልከቱ::

ማስታወሻ:- የማያምን ሰው ኢየሱስን በእውነት ሊመስለው አይችልም:: አንድ ሰው ይህንን ቢሞክር ውርደት ይከተለዋል:: ማንም ሰው ኢየሱስን እንደሚመስል በማስመሰል ክርስቲያን ሊሆን አይችልም:: ደኅንነት በጸጋና በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው:: ነገር ግን አንተ ክርስቲያን ከሆንክ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ልትመስለው ይገባል፣ ትችላለህም::

1. **ሁሉም ክርስቲያን ክርስቶስን ይመስል ዘንድ ተመርጧል፣ ተጠርቷልም::**

ሮሜ 8:29-30:: «እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው፤ ይኸውም ከብዙ ወንድሞች መካከል እርሱ በኵር እንዲሆን ነው:: አስቀድሞ የወሰናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውን አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውን አከበራቸው::»

2. **ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር መልክ ታድሰዋል፣ ክርስቶስንም ወደ መምሰል ሁልጊዜ ይለወጣሉ::**

2ኛ ቆሮ. 3:18:: «እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እንደመስተዋት እያንጸባረቅን፣ የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፤ ይህም የሚሆነው መንፈስ ከሆነ ጌታ ነው::»

ቈላ. 3:9-10:: «አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር አውልቃችሁ ስለ ጣላችሁ እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ:: የፈጣሪውን መልክ እንዲመስል በዕውቀት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችኋል::

ኤፌ. 4:22-24:: «ቀድሞ ስለ ነበራችሁበት ሕይወትም፣ በሚያታልል ምኞቱ የጎደፈውን አሮጌ ሰውነታችሁን አውልቃችሁ እንድትጥሉ ተምራችኋል፤ ደግሞም በአእምሮአችሁ መንፈስ እንድትታደሱ፣ እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና



እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው::»

3. **ኢየሱስን መምሰል አለብን፤ ልክ እርሱ እንደሚመላለሰው መመላለስ አለብን::**

1ኛ ዮሐ. 2:6:: «ማንም በእርሱ እኖራለሁ የሚል፣ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል::»

4. **ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን በመምሰል አብዝተን ወደ እርሱ መልክ እንድንቀርብ ይጋብዘናል::**

ዮሐ. 13:2-11:: (ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር እያጠበ ሳለ፣ ሆን ብሎ በዓላማ ምሳሌን ተወላቸው::)

ዮሐ. 13:12-15:: «እግራቸውን አጥቦ ካበቃ በኋላም፣ ልብሱን ለብሶ ተመልሶ በቦታው ተቀመጠ፤ እንዲህም አላቸው፤ «ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን? እናንተ፣ «መምህርና፣ ጌታ» ትሉኛላችሁ፤ ትክክል ነው፤ እንደምትሉኝ እንዲሁ ነኝና:: እንግዲህ እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ሆኜ ሳለሁ እግራችሁን ካጠብሁ፣ እናንተም እንደዚሁ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ ይገባችኋል:: እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናንተም እንደዚሁ እንድታደርጉ ምሳሌ ትቼላችኋለሁ::»

5. **ጳውሎስ ለሌሎች በረከት እንሆን ዘንድ ኢየሱስን እንድንመስል ያዝዘናል::**

ሮሜ 15:1-3:: «እኛ ብርቱዎች የሆንን፣ የደካሞችን ጕድለት መሸከም እንጂ ራሳችንን ማስደሰት የለብንም:: እያንዳንዳችን ባልንጀራችንን ለማነጽ፣ እርሱንም ለመጥቀም ደስ የሚያሰኘውን ነገር ማድረግ ይገባናል፤ ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና፤ ነገር ግን፣ «አንተን የሰደቡበት ስድብ በእኔ ላይ ደረሰብኝ» ተብሎ እንደ ተጻፈው ሆነበት::»

ኤፌ. 5:1-2:: «እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን ምሰሉ፤ ክርስቶስ እንደ ወደደን ራሱንም ስለ እኛ መልካም መዐዛ ያለው መባና መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር እንደ ሰጠ

እናንተም በፍቅር ተመላለሱ»

6. አንድ ሰው ክፉ ነገር ሲያደርግብን፣ ኢየሱስን መምሰል አለብን:: እርሱ ባለ መበቀል ወይም ብድር ባለመመለስ እኛ የምንከተለውን ምሳሌ ትቶልናል::

1ኛ ጴጥ. 2:18-23::

1ኛ ጴጥ. 2:20-21:: «ክፉ ሥራ ሠርታችሁ ብትቀጡና ብትታገሡ ምን ምስጋና ይኖራችኋል? ነገር ግን መልካም ሥራ ሠርታችሁ መከራ ብትቀበሉና ብትታገሡ ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ያስገኝላችኋል:: የተጠራችሁትም ለዚሁ ነው፤ ምክንያቱም ክርስቶስ ስለ እናንተ መከራን የተቀበለው የእርሱን ፈለግ እንድትከተሉ ምሳሌን ሊተውላችሁ ነው::»

7. ጳውሎስ ለሌሎች ክርስቲያኖች ጥሩ ምሳሌ ይሆን ዘንድ ኢየሱስን መሰለ::

1ኛ ቆሮ. 11:1:: «እኔ የክርስቶስን ምሳሌ እንደምከተል እናንተም የእኔን ተከተሉ::»

8. የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በከፊል ኢየሱስንና ደቀ መዛሙርቱን በመምሰል ለሌሎች ጥሩ ምሳሌ ሆነውላቸዋል::

1ኛ ተሰ. 1:6-7:: «እናንተ እኛንና ጌታን መስላችኋል፤ ምንም እንኳ ብርቱ መከራ ቢደርስባችሁም ቃሉን በመንፈስ ቅዱስ ደስታ ተቀብላችኋል:: ከዚህም የተነሣ በመቄዶንያና በአካይያ ለሚገኙ ምእመናን መልካም ምሳሌ ሆናችኋል::»

9. ክርስቶስን የሚመስል መታዘዝ ክርስቶስን የሚመስለውን መለኮታዊ ፍቅር ማጣጣሚያና ደስታችሁን ፍጹም የምታደርጉበት መንገድ ነው::

ዮሐ. 15:9-11:: «አብ እንደ ወደደኝ ሁሉ እኔም ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ:: እኔ የአባቴን ትእዛዝ ጠብቄ በፍቅሩ እንደምኖር እናንተም ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ:: ደስታዬ በእናንተ እንዲሆንና ደስታችሁም ሙሉ እንዲሆን ይህን ነግሬአችኋለሁ::»



10. ኢየሱስን ፊት ለፊት የምናይበትና ሙሉ ለሙሉ እርሱን ወደ መምሰል የምንለወጥበት እርግጠኛ ተስፋ እርሱ ቅዱስ እንደሆነ ሁሉ እኛም መቀደስን እንድንፈልግ ሊያነሣሣን ይገባል::

1ኛ ዮሐ. 3:2-3:: «ወዳጆች ሆይ፤ እኛ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ወደ ፊት ምን እንደምንሆን ገና አልተገለጠም:: እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እናየዋለንና፣ እርሱን እንደምንመስል እናውቃለን:: በእርሱ ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ፣ እርሱ ንጹሕ እንደሆነ ራሱን ያነጻል::»

11. የትንሣኤው አዳኝ ለእግዚአብሔር ይኖራል:: እኛም ከክርስቶስ ጋር ሞትን የተነሣን ሁሉ ይህንኑ ማድረግ አለብን::

ሮሜ 6:10-14::

ሮሜ 6:10-12:: «በሞተ ጊዜ፣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለኀጢአት ሞቶአል፤ ነገር ግን በሕይወት መኖርን ለእግዚአብሔር ይኖራል:: እንደዚሁም ለኀጢአት እንደ ሞታችሁ፣ ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቍጠሩ:: ስለዚህ ክፉ መሻቱን ትፈጽሙ ዘንድ በሟች ሥጋችሁ ላይ ኀጢአት እንዲነግሥበት አታድርጉ::»

# ሌሎችን መውደድና ማገልገል

በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያንን፣ የቅዱሳንን ኅብረት ከገጽ 37 ኢየሱስን መምሰልን በገጽ 114 እና እግዚአብሔርን መውደድን በገጽ 124 ተመልከቱ::

1. እግዚአብሔር ለእኛ ላለው ፍቅር ምላሽ በሚሆን መልኩ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ::

   1ኛ ዮሐ. 4:9-21::

   1ኛ ዮሐ. 4:9-11:: «እግዚአብሔር ፍቅሩን በመካከላችን የገለጠው እንዲህ ነው፤ እኛ በእርሱ አማካይነት በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ወደ ዓለም ላከ:: ፍቅር ይህ ነው፤ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው ሳይሆን እርሱ እንደወደደንና ስለ ኀጢአታችን ማስተሰረያ ይሆን ዘንድ ልጁን መላኩ ነው:: ወዳጆች ሆይ እግዚአብሔር እንዲህ ከወደደን፣ እኛም እርስ በእርሳችን መዋደድ ይገባናል::»

   1ኛ ዮሐ. 4:21:: «እርሱም «እግዚአብሔርን የሚወድ ሁሉ ወንድሙን መውደድ ይገባዋል» የሚለውን ይህን ትእዛዝ ሰጥቶናል::

2. እርስ በርሳችሁ በጥልቅ ተዋደዱ::

   1ኛ ጴጥ. 1:22:: «እንግዲህ ለእውነት በመታዘዝ ነፍሳችሁን ስላነጻችሁ፣ ለወንድሞቻችሁ ቅን ፍቅር ይኑራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም አጥብቃችሁ ከልብ ተዋደዱ::»

   1ኛ ጴጥ. 4:8:: «ፍቅር ብዙ ኀጢአትን ይሸፍናልና ከሁሉ በላይ እርስ በርሳችሁ ከልብ ተዋደዱ፤»

3. እውነተኛ ፍቅር ሌሎችን ማገልገል ነው::

   1ኛ ጴጥ. 4:9-10:: «እርስ በርሳችሁ ያለ ማጉረምረም እንግድነት ተቀባበሉ:: እንደ ታማኝ የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ መጋቢ እያንዳንዱ ሰው በተቀበለው የጸጋ ስጦታ ሌላውን ያገልግል፤»

4. ፍቅር እጅግ አስፈላጊና መሠረታዊ ጉዳይ ነው፤ ማንም ሰው ያለ እርሱ ሊኖር አይችልም::



   1ኛ ቆሮ. 13:1-3::

5. ጳውሎስ ፍቅር ምን እንሆነ ይገልጻል::

   1ኛ ቆሮ. 13:4-7:: «ፍቅር ታጋሽ ነው፤ ደግሞም ቸር ነው:: ፍቅር አይመቀኝም፤ አይመካም፤ አይታበይም፤ ተገቢ ያልሆነ ነገር አያደርግም፤ ራስ ወዳድ አይደለም፤ አይበሳጭም፣ በደልን አይቈጥርም:: ፍቅር ከእውነት ጋር እንጂ በዐመፅ ደስ አይለኝም:: ፍቅር ሁልጊዜ ይታገሣል፤ ሁልጊዜ ያምናል፤ ሁል ጊዜ ተስፋ ያደርጋል፤ ሁልጊዜ ጸንቶ ይቆማል::»

6. መውደድ ለእርስ በርስ መስጠት ነው::

   ሮሜ 12:9-10:: «ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን፤ ክፉ የሆነውን ሁሉ ተጸየፉ፤ በጎ ከሆነው ነገር ጋር ተቈራኙ:: እርስ በርሳችሁ በወንድማማች መዋደድ አጥብቃችሁ ተዋደዱ፤ አንዱ ሌላውን ከራሱ በማስበለጥ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ::»

7. ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር በማጠብ እርስ በርሳችን እንዴት መዋደድ እንዳለብን ምሳሌ ተወልን::

   ዮሐ. 13:2-17::

   ዮሐ. 13:14-15:: «እንግዲህ እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ሆኜ ሳለሁ እግራችሁን ካጠብሁ፣ እናንተም እንደዚሁ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ ይገባችኋል:: እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናንተም እደዚሁ እንድታደርጉ ምሳሌ ትቼላችኋለሁ::»

8. ኢየሱስ እርሱን እንድንመስል፣ ልክ እርሱ በወደደን መልክ እኛ ም ሌሎችን እንድንወድድ አዘዘን::

   ማቴ. 16:24:: ከዚያም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፤ «ሊከተለኝ የሚወድ ራሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ::»

   ዮሐ. 13:34:: «አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ ይኸውም እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ነው፤ እንግዲህ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ...»

ዮሐ. 15:12:: «ትእዛዜን ይህች ናት፤ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ::»

9. ግለኞች (ራስ ወዳዶች አትሁኑ)፣ ነገር ግን ሌሎችንም በመመልከት ኢየሱስን ምሰሉ::

ፊል 2:3-5:: «ሌሎች ከእናንተ እንደሚሻሉ በትሕትና ቍጠሩ እንጂ፣ በራስ ወዳድነት ምኞት ወይም ከንቱ ውዳሴ ለማግኘት አንዳች አታድርጉ:: እያንዳንዳችሁ ሌሎችን የሚጠቅመውንም እንጂ፣ ራሳችሁን የሚጠቅመውን ብቻ አትመልከቱ:: በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ፣ በእናንተም ዘንድ ይሁን::»

10. ኢየሱስ ሁለንተናውን ሰጠን::

ፊል. 2:6-8::

11. ክብርንና አንቱታን አትፈልጉ፣ ይልቁንም፣ እንደ ኢየሱስ ሆናችሁ ሌሎችን ለማገልገል ተዘጋጁ::

ማቴ. 20:20-28::

ማቴ. 20: 26-28:: «በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም:: ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን፤ የበላይ ለመሆን የሚሻም የእናንተ የበታች ይሁን፤ የሰው ልጅ እንዲያገለግሉት ሳይሆን፣ ለማገልገልና ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት መጥቶአልና::»

12. ለሌሎች ፍላጐት መገኘት ለክርስቶስ ማድረግ ነው::

ማቴ. 25:34-40::

ማቴ. 25:35-36:: «ምክንያቱም ተርቤ አብልታችሁኛል፤ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል፤ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛል፤ ታርዤ አልብሳችሁኛል፤ ታምሜ አስታምማችሁኛል፤ ታስሬ ጠይቃችሁኛ ል::»

ማቴ. 25:40:: «ንጉሡም መልሶ፣ <እውነት እላችኋለሁ፣ ከእነዚህም አነስተኛ ከሆኑት ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት፣ ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው> ይላቸዋል::



13. መልካምን ለማድረግ አትታክቱ::

ገላ. 6:9:: «በጎ ነገር ከማድረግ አንታክት፤ ተስፋ ካልቈረጥን ጊዜው ሲደርስ መከሩን እናጭዳለን::»

14. ለሁሉም በተለይም ለሃይማኖት ቤተሰብ መልካምን አድርጉ::

ገላ. 6:10:: ስለዚህ ዕድሉ ካለን ለሰው ሁሉ፣ በተለይም ለእምነት ቤተ ሰቦች መልካም እናድርግ::

15. ወርቃማውን ሕግ ተከተሉ::

ማቴ. 7:12:: «ሌሎች እዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ነገር እናንተም አድርጉላቸው፤ ኦሪትም፣ ነቢያትም በዚህ ይጠቃለላሉና::»

16. ራስ ወዳዶች አትሁኑ፣ነገር ግን ሌሎንም ደስ አሰኙ::

ሮሜ 15:1-2:: «እኛ ብርቱዎች የሆን፣ የደካሞችን ጕድለት መሸከም እንጂ ራሳችንን ማስደሰት የለብንም:: እያንዳንዳችን ባልንጀራችንን ለማነጽ፣ እርሱንም ለመጥቀም ደስ የሚያሰኘውን ነገር ማድረግ ይገባናል::»

17. ኢየሱስን ምሰሉ::

ሮሜ 15:3:: «ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና፤ ነገር ግን፣ «አንተን የሰደቡበት ስድብ በእኔ ላይ ደረሰብኝ» ተብሎ እንደ ተጻፈው ሆነበት::»

18. መልካም ለማድረግ ራሳችሁን አስገዙ::

ቲቶ 3:14:: ከእኛ ወገን ለሆኑት ለዕለት የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገኙና ኑሮአቸውም ፍሬ የሌለው እንዳይሆን ለመልካም ሥራ መትጋትን ይማሩ ዘንድ ይገባቸዋል::

19. መልካም በማድረግ ሕይወታችሁን ልታገኙ ትችላላችሁ::

ማቴ. 10:39:: «ሕይወቱን ሊያድን የሚፈልግ ያጠፋታል፤ ሕይወቱን ስለ እኔ አሳልፎ የሚሰጥ ግን ያገኛታል::»

20. ጠላቶቻችሁንና የሚያሳድዷችሁን ውደዱ::

ማቴ. 5:43-48:: «ወዳጅህን ውደድ፤ ጠላትህን ጥላ» እንደ ተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ:: እላችኋለሁ:: እንደዚህም በማድረጋችሁ በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆናላችሁ፤ እርሱ ፀሓዩን ለክፉዎችና ለደጎች ያወጣል፤ ዝናቡንም ለኀጢአተኞችና ለጻድቃን ያዘንባል:: የሚወዷችሁን ብቻ የምትወዱ ከሆነ ምን ዋጋ ታገኛላችሁ? ቀራጮችስ ይህንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁን ብቻ እጅ የምትነሡ ከሆነ ከሌሎች በምን ትሻላላችሁ? አሕዛብስ ይህንኑ ያደርጉ የለምን? ስለዚህ የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ::»

ሮሜ 12:20-21:: «ይልቁንስ፣ «ጠላትህ ቢራብ አብላው፤ ቢጠማም አጠጣው:: ይህን በማድረግህም የእሳት ፍም በራሱ ላይ ትከምራለህ::» ክፉን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ::»

**21. እንደ ክርስቶስ አካል ክፍሎች፣ ሁላችንም ለሁላችንም እናስፈልጋለን፤ እያንዳንዱም የአካል ክፍል (አባል) ሌሎችን ለማሳደግ የራሱን የጸጋ ስጦታ ሊጠቀም ያስፈልገዋል::**

1ኛ ቆሮ. 12:1-31::

1ኛ ቆሮ. 12:4-7:: «ስጦታዎች ልዩ ልዩ ሲሆኑ፣ መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ጌታ ግን አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ሁሉን በሁሉ የሚሠራው ግን ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው:: ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው::»

1ኛ ጴጥ. 4:10-11:: «እንደ ታማኝ የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ መጋቢ እያንዳንዱ ሰው በተቀበለው የጸጋ ስጦታ ሌላውን ያገልግል፤ ከእናንተ ማንም የሚናገር ቢኖር እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር:: የሚያገለግልም ቢኖር እግዚአብሔር በሚሰጠው ብርታት ያገልግል፤ ይኸውም እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እንዲከብር ነው፤ ክብርና ኀይል ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን አሜን::»

**22. እውነተኛ እርነት አንዱ ሌላውን በፍቅር ማገልገል ነው::**



ገላ. 5:13-15:: «ወንድሞቼ ሆይ፤ ነጻ እንድትሆኑ ተጠርታችኋል፤ ነጻነታችሁን ግን ሥጋዊ ምኞታችሁን መፈጸሚያ አታደርጉ፤ ይልቁንም አንዱ ሌላውን በፍቅር ያገልግል:: ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ተጠቃሎአል፤ ይኸውም፣ «ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» የሚል ነው:: ነገር ግን እርስ በርሳችሁ የምትነካከሱና የምትበላሉ ከሆነ፣ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ::»

1ኛ ተሰ. 4:9-11:: «ስለ ወንድማማች መዋደድ ማንም እንዲጽፍላችሁ አያስፈልግም፤ ምክንያቱም እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ እናንተ ራሳችሁ ከእግዚአብሔር ተምራችኋልና:: በመላዪቱ መቄዶንያ የሚገኙትን ወንድሞች ሁሉ እንደምትወዷቸው የታወቀ ነው፤ ነገር ግን ወንድሞች ሆይ፤ ከዚህ በበለጠ እንድትገፉበት እንመክራችኋለን:: ከዚህ በፊት እንዳዘዝናችሁ በገዛ እጃችሁ ሥሩ፤ በጸጥታ ኑሩ፤ በራሳችሁ ጉዳይ ላይ ብቻ አተኩሩ::»

**23. *መልካሙን ሳምራዊ ሁኑ:: እግዚአብሔር በመንገዳችሁ ላይ የሚያስቀምጣቸውን ችግረኛ ሰዎች እርዱ::***

*ሉቃ. 10:25-37:: (የደጉ ሳምራዊ ታሪክ)*

*ሉቃ.* 10:36-37:: « «እንግዲህ፣ ከእነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ሰው ባልንጀራ የሆነው የትኛው ይመስልሃል?» ሕግ ዐዋቂውም «የራራለት ነዋ» አለ:: ኢየሱስም፣ «አንተም ሂድና እንዲሁ አድርግ» አለው::

**24. ተራ ንግግርና በጎ አስተሳሰብ ብቻውን ምንም የሚፈይደው ነገር የለም:: ተንቀሳቀሱ! መልካም የሆነውን አድርጉ!**

1ኛ ዮሐ. 3:16-18:: «ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ስለ እኛ አሳልፎ ስለ ሰጠ፣ ፍቅር ምን እንደሆነ በዚህ እናውቃለን፣ እኛም ሕይወታችንን ስለ ወንድሞቻችን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባናል:: ማንም ሀብት እያለው፣ ወንድሙ ሲቸገር አይቶ ባይራራለት፣ የእግዚአብሔር ፍቅር እንዴት በእርሱ ይኖራል? ልጆች ሆይ፤ በተግባርና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት ብቻ አንዋደድ::»

ያዕ. 2:15-17:: «አንድ ወንድም ወይም አንዲት እኅት የሚለብሱት ልብስም ሆነ የሚመገቡት ምግብ አጥተው፣ ከእናንተ መካከል አንዱ፣ «በሰላም ሂዱ፤ አይብረዳችሁ፤ ጥገቡ» ቢላቸው፣

ለሰውነታቸው ግን የሚያስፈልጋቸውን ባይሰጣቸው፣ ምን ይጠቅማቸዋል? እንዲሁ ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው።»

**25. ማድረግ የሚገባህን መልካም ነገር ታውቃለህ? አድርገው፣ አለበለዚያ ትበድላለህ።**

*ያዕ.* 4:17። «እንግዲህ መልካም የሆነውን ነገር ማድረግ እንዳለበት እያወቀ የሚያደርግ ሰው ኀጢአት ያደርጋል።»



# እግዚአብሔርን መውደድ

በተጨማሪ መታዘዝን በገጽ 136፣ ሌሎችን መውደድና ማገልገልን በገጽ 118፣ ኃጢአትን ማሸነፍን በገጽ 142 እና እድገታዊ ቅድስናን በገጽ 170 ላይ ተመልከቱ።

**1. አማኙ ለእግዚአብሔር ፍቅርና ሞገስ ምላሽ ይሰጣል።**

ዘዳ. 6:4-7። «እስራኤል ሆይ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) አንድ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነው። አምላክህን እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስ፣ በፍጹም ኀይልህ ውደድ። ዛሬ የምሰጥህን እነዚህን ትእዛዛት በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስጠናቸው፤ በቤትህ ስትቀመጥ፣ በመንገድም ስትሄድ፣ ስትተኛና ስትነሣም ስለ እነርሱ ተናገር።»

**2. ኢየሱስ፣ እግዚአብሔርን ከሁሉም ነገር በላይ እንድንወድ ይጠራል። እርሱም ሕጉን እንደ ፍቅር ጉዳይ አድርጉ ያጠቃልለዋል።**

ማቴ. 22:37-40። «እርሱም እንዲህ አለው፤ «<ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤> ይህ የመጀመሪያውና ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ ነው፤ ሁለተኛውም ያንኑ ይመስላል፤ ይህም፣ <ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ> የሚለው ነው፤ ሕግና ነቢያት በሙሉ በእነዚህ ሁለት ትእዛዛት ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው።» »

**3. ክርስቶስ ለእኛ ያለው ፍቅር እርሱን እንድንወድደውና እንድናገለግለው ሊያስገድደን ይገባል።**

2ኛ ቆሮ. 5:14-15። «የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና፤ ምክንያቱም አንዱ ስለ ሁሉ እንደ ሞተ እርግጠኞች ሆነናል፣ ከዚህም የተነሣ ሁሉ ሞተዋል። በሕይወት ያሉትም ለሞተላቸውና ከሙታን ለተነሣላቸው እንጂ ከእንግዲህ ለራሳቸው እንዳይኖሩ እርሱ ስለ ሁሉ ሞተ።»

**4. ከጌታ ጋር ተጣበቁ፣ ከፍቅርም የተነሣ ትእዛዛቱን ጠብቁ።**

ኢያሱ 22:5። የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ፣ አምላካችሁን እግዚአብሔርን እንድትወዱ፣ በመንገዱ ሁሉ እንድትሄዱ፣ ትእዛዙን እንድትፈጽሙ፣ እርሱም አጥብቃችሁ እንድትይዙት እንዲሁም በፍጹም ልባችሁ፣ በፍጹም ነፍሳችሁ እንድታገለግሉት የሰጣችሁን

ትእዛዙንና ሕጉን ነቅታችሁ ጠብቁ::

**5. ኢየሱስን መውደድ ትምህርቱን መታዘዝ ነው::**

ዮሐ. 14:23-24:: «ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤ ወደ እርሱ እንመጣለን፤ ከእርሱም ጋር እንኖራለን:: የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም:: ይህ የምትሰሙት ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም::»

**6. ሰሎሞን፣ ለእግዚአብሔር ሞገስ ከልባችን የሆነ አገልግሎትን በመስጠት ምላሽ እንድንሰጥ ይነግረናል::**

1ኛ ነገ. 8:56-61::

1ኛ ነገ. 8:61:: «ስለዚህ እንደ ዛሬው ዕለት ሁሉ፣ በሥርዐቱ እንድትኖሩና ትእዛዙን እንድትጠብቁ ልባችሁ ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር የተገዛ ይሁን::»

**7. ዳዊት ልጁ ሰሎሞን ሙሉ ለሙሉ በተሰጠ ልብ እግዚአብሔርን ያገለግለው ዘንድ የሰጠው ትእዛዝ ለሁላችንም መልካም ነው::**

1ኛ ዜና 28:9 «አንተም ልጄ ሰሎሞን ሆይ፤ እግዚአብሔር ልብን ሁሉ ስለሚመረምርና ሐሳቡን ሁሉ ስለሚያውቅ፣ የአባትህን አምላክ ዕወቅ፤ በፍጹም ልብና በበጎ ፈቃድ አገልግለው:: ከፈለግኸው ታገኘዋለህ፤ ከተውከው ግን እርሱም ለዘላለም ይተውሃል::»

**8. በፍቅር አነሣሽነት መከፋፈልንና ሁሉንም ኃጢአተኛ ተፈጥሮዎች አስወግዱ:: ይልቁንም ክርስቶስን ልበሱ::**

ሮሜ 13:13-14:: «በቀን እንደምንመላለስ በአግባብ እንመላለስ:: በጭፈራና በስካር አይሁን፤ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፤ በክርክርና በቅናትም አይሁን:: ይልቁንም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም ይፈጽም ዘንድ ለሥጋ በሐሳባችሁ አትመቻቹለት::»

**9. እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር ለንጽሕና እንድንተጋ ሊያንቀሳቅሰን ይገባል::**

2ኛ ቆሮ.7:1:: «እንግዲህ፣ ወዳጆች ሆይ፤ ይህ የተስፋ ቃል ስላለን፣ ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን እናንጻ፤ እግዚአብሔርንም በመፍራት ቅድስናችንን ፍጹም እናድርገው::



# ሴሰኝነት፣ ክፉ ምኞቶች

**1. የሔዋን ኃጢአት የጀመረው በምኞት ነው::**

ዘፍ. 3:6:: «ሴቲቱ የዛፉ ፍሬ ለመብል መልካም፣ ለዐይን የሚያስደስትና ጥበብንም ለማግኘት የሚያጓጓ እንደሆነ ባየች ጊዜ፣ ከፍሬው ወስዳ በላች፤ ከእርሷም ጋር ለነበረው ለባሏ ሰጠችው፤ እርሱም በላ::»

**2. አትመኙ::**

ዘፀ. 20:17:: «የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት ወይም የእርሱን ወንድ አገልጋይ ሆነ ሴት አገልጋይ፣ በሬውንም ሆነ አህያውን ወይም የእርሱ የሆነውን ማናቸውንም ነገር አትመኝ::»

**3. የኃጢአተኛ ተፈጥሮአችሁን ምኞት እንዴት እንደምታረኩ አታስቡ::**

ሮሜ 13:14:: «ይልቁንም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም ይፈጽም ዘንድ ለሥጋ በሐሳባችሁ አትመቻቹለት::»

**4. ለዓለማዊ ምኞቶቻችሁ እምቢ በሉ::**

ቲቶ 2:11-12:: «ድነት የሚገኝበት የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰዎች ሁሉ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ በኀጢአት መኖርንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን፣ በአሁኑ ዘመን ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ፣ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት እንድንኖር ያስተምረናል፤»

**5. ክፉ ምኞትን የሚፈጽሙ ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣ ሰለባዎች ናቸው::**

ኤፌ. 2:3:: «እኛ ሁላችን በአንድ ወቅት የሥጋችንን ምኞት እያረካን፣ መንገዱንም እየተከተልን በመካከላቸው እንኖር ነበር፤ እንደ ሌሎቹም የቍጣ ልጆች ነበርን::»

**6. ክርስቶስ ከሴሰኝነትና ከክፉ ምኞት ሊያድነን መጣ::**

ኤፌ. 2:4-5:: «ነገር ግን በምሕረቱ ባለ ጠጋ የሆነ እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ፣ በበደላችን ሙታን ሆነን ሳለ፣

በክርስቶስ ሕያዋን አደረገን፤ የዳናችሁት በጸጋ ነው፡፡»

7. ክፉ ምኞቶቻችሁን አትከተሉ፣ ነገር ግን ቅዱሳን ሁኑ፡፡

1ኛ ጴጥ. 1:14-16:: «ታዛዦች ልጆች እንደ መሆናችሁ መጠን ቀድሞ ባለማወቅ ትኖሩበት የነበረውን ክፉ ምኞት አትከተሉ:: ነገር ግን የጠራችሁ እርሱ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተም በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፤» ምክንያቱም «እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ተብሎ ተጽፎአል፡፡»

1ኛ ጴጥ. 2:11:: «ወዳጆች ሆይ፤ በዚህ ዓለም እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ መጠን፣ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት እንድትርቁ እለምናችኋለሁ፡፡»

8. የሥጋን ምኞት ለማሸነፍ በመንፈስ ኑሩ፡፡

ገላ. 5:16:: «እንግዲህ በመንፈስ ኑሩ እላለሁ፤ የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙም፡፡»

9. እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ ልባቸውን በሥጋ ፍላጐት ላይ ያሳርፋሉ፡፡

ሮሜ 8:5-8:: እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ ልባቸውን በሥጋ ፍላጎት ላይ ያሳርፋሉ፤ እንደ መንፈስ የሚኖሩ ግን ልባቸውን በመንፈስ ፍላጎት ላይ ያደርጋሉ፡፡ የሥጋን ነገር ማሰብ ሞት ነው፤ የመንፈስን ነገር ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው:: ለኀጢአት የተገዛ አእምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ ነው፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛም፤ መገዛትም አይችልም፡፡ በሥጋ የሚመሩትም እግዚአብሔርን ማስደሰት አይችሉም፡፡



# ጋብቻ፣
## የባልና ሚስት ግንኙነቶች

በተጨማሪ አስታራቂዎችና ሰላም ጠባቂዎች በገጽ 151 ተመልከቱ፡፡

1. ጋብቻ የተጠነሰሰውና የተቋቋመው በእግዚአብሔር ነው፡፡

ዘፍ. 2:18-25::

2. በጋብቻ ውስጥ ባልና ሚስት ሊያሳድጉት የሚገባቸው ቁልፍ ነገር ኅብረትና ቅርበት ነው፡፡

ዘፍ. 2:18፣24:: «ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም)፣ «ሰው ብቻውን መሆኑ መልካም አይደለምና የሚስማማውን ረዳት አበጅለታለሁ» አለ:: ...ስለዚህ ሰው ከአባቱና ከእናቱ ተለይቶ ከሚስቱ ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፡፡»

3. በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ካለው ግንኙነት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

ኤፌ. 5:23:: «ክርስቶስ አካሉ ለሆነችውና አዳኝ ለሆናት ቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ባልም የሚስቱ ራስ ነውና፡፡

ኤፌ. 5:31-32:: «ስለዚህም ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር አንድ ይሆናሉ፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ»:: ይህ ጥልቅ ምሥጢር ነው፤ እኔም ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እናገራለሁ፡፡»

4. ባል የሚስትና የቤት ራስ ነው፡፡

ኤፌ. 5:23:: «ክርስቶስ አካሉ ለሆነችውና አዳኟ ለሆናት ቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ባልም የሚስቱ ራስ ነውና፡፡»

5. ባሎች ሚስቶቻቸውን ልክ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት አድርገው መውደድ አለባቸው፡፡

ኤፌ. 5:25:: «ባሎች ሆይ፣ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳትና ራሱንም ስለ እርሷ አሳልፎ እንደ ሰጠ፣ እናንተም

ሚስቶቻችሁን ውደዱ::»

6. ባሎች በፍቅር ራስነታቸውን መተግበር አለባቸው::

ኤፌ. 5:25-33::

ቈላ. 3:19:: «ባሎች ሆይ፤ ሚስቶቻችሁን ውደዱ፣ መራራም አትሁኑባቸው::»

7. ባሎች ሚስቶቻቸውን በፍቅርና የእግዚአብሔርን ስጦታ እኩል አብረዋቸው እንደሚወርሱ አድርገው ሊመለከቷቸው ይገባል::

1ኛ ጴጥ. 3:7:: «ባሎች ሆይ፤ እናንተም ደግሞ ጸሎታችሁ እንዳይነቀፍ በኑሮአችሁ ሁሉ ለሚስቶቻችሁ አስቡላቸው፣ ደካሞች ስለሆኑና የሕይወትንም በረከት አብረዋችሁ ስለሚወርሱ አክብሯቸው::»

8. ባል የገዛ ራሱን ቤት በሚገባ ማስተዳደር አለበት፤ እርሱ አስተዳዳሪው ነው::

1ኛ ጢሞ. 3:4:: «ልጆቹን ታዛዥና አክባሪ አድርጎ በማሳደግ የገዛ ቤተ ሰቡን በአግባቡ የሚያስተዳደር ሊሆን ይገባል::»

9. ባልና አባት በመጀመሪያ ደረጃ ልጆችን የማስተማር ኃላፊነት አለበት::

ኤፌ. 6:4:: «አባቶች ሆይ፤ እናንተም ልጆቻችሁን አታስቈጧቸው፤ ነገር ግን በጌታ ምክርና ተግሣጽ አሳድጓቸው::»

ልጆችን ማሠልጠን የሚለውንም በገጽ 220 ላይ ተመልከቱ::

10. እግዚአብሔር ለሚስት ያለው ዕቅድ፣ ለባሏ የምትመች ረዳት እንድትሆን ነው::

ዘፍ. 2:18:: «ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) «ሰው ብቻውን መሆኑ መልካም አይደለምና የሚስማማውን ረዳት አበጅለታለሁ» አለ::

11. ባልና ሚስት ሁለቱም የክርስቶስንና የቤተ ክርስቲያንን ግንኙነት ለማንጸባረቅ መፈለግ አለባቸው::

ኤፌ. 5:25፣32::



12. ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ፣ ሚስት ለባሏ መገዛት አለባት::

ኤፌ. 5:22-24:: «ሚስቶች ሆይ፤ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁም ተገዙ ክርስቶስ፣ አካሉ ለሆነችውና አዳኟ ለሆናት ቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ባልም የሚስቱ ራስ ነውና::» እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ፣ ሚስቶችም ለባሎቻቸው በማንኛውም ነገር እንደዚሁ መገዛት ይገባቸዋል::

ቈላ. 3:18:: «ሚስቶች ሆይ፤ በጌታ ዘንድ ተገቢ በመሆኑ ለባሎቻችሁ ታዘዙ::»

1ኛ ጴጥ. 3:1-2:: «ሚስቶች ሆይ፤ እናንተም እንደዚሁ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ አንዳድ ለቃሉ የማይታዘዙ ቢኖሩ፣ ያለ ቃል በሚስቶቻቸው አኗኗር ተማርከው ይመለሳሉ፤ ይህም የሚሆነው ንጹሕና ፍጹም አክብሮት የተሞላውን ኑሮአችሁን ሲመለከቱ ነው::»

13. ሴት በወንድ ላይ ልትሠለጥን አይገባም::

1ኛ ጢሞ. 2:11-14:: «ሴት በጸጥታና በሙሉ መገዛት ትማር:: ሴት ዝም እንድትል እንጂ እንድታስተምር ወይም በወንድ ላይ ሥልጣን እንዲኖራት አልፈቅድም:: ምክንያቱም አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአል፤ ከዚያም ሔዋን ተፈጠረች:: ደግሞም የተታለለው አዳም አይደለም፤ የተታለለችውና ኀጢአተኛ የሆነችው ሴቷ ናት::»

14. መጽሐፍ ቅዱስ ተሰጥኦዋን በታማኝነት ለምትጠቀመው ልባም ሴት ገለጻ ይሰጠናል::

ምሳ. 31:10-31::

ምሳ. 31:10-11:: «ጠባየ መልካምን ሚስት ማን ያገኛታል? ከቀይ እንቍ እጅግ ትበልጣለች:: ባሏ ሙሉ በሙሉ ይተማመንበታል፤ የሚጐድልበትም ነገር የለም::»

15. ከአካላዊ ውበት ይልቅ እግዚአብሔርን መፍራት ጠቃሚ ነው::

ምሳ. 31:30:: «ቍንጅና አታላይ ነው፣ ውበትም ይረግፋል፤ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን የተመሰገነች ናት::»

1ኛ ጴጥ. 3:3-4:: «ውበታችሁ በውጫዊ ነገሮች በመሸምንሞን ይኸውም ሹሩባ በመሠራት፣ በወርቅ በማጌጥና በልብስ አይሁን፤ ነገር ግን ውበታችሁ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ፣ ገርና ጭምት መንፈስ ያለበት፣ ምንጊዜም የማይጠፋ የውስጥ ሰውነት ውበት ይሁን::

**16. ባሎችና ሚስቶች መጣላትና እርስ በርስ መጠፋፋት የለባቸውም::**

ገላ. 5:15:: «ነገር ግን እርስ በርሳችሁ የምትነካከሱና የምትበላሉ ከሆነ፣ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ::»

**17. ባልና ሚስት ሁለቱም ችግር በመጣ ጊዜ ወዲያውኑ ሰላምን መከታተል አለባቸው::**

ማቴ. 5:23-24:: «ስለዚህ መባህን በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር በምታቀርብበት ጊዜ ወንድምህ የተቀየመብህ ነገር መኖሩ ትዝ ቢልህ፣ መባህን በዚያው በመሠዊያው ፊት ተወው፤ በመጀመሪያ ሄደህ ከወንድምህ ጋር ተስማማ፤ ከዚያም ተመልሰህ መባህን ለእግዚአብሔር አቅርብ::»

**18. እርስ በእርሱ የተከፋፈለ ቤት አይቆምም::**

ማቴ. 12:25:: «ኢየሱስም ሐሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ አላቸው፤ «እርስ በርሱ የተከፋፈለ መንግሥት ሁሉ ይወድቃል፤ እርስ በእርሱም የተከፋፈለ ከተማ ወይም ቤት አይጸናም::»

**19. ከእናንተ አስተሳሰብ ፈጽሞ የራቁትን መውደዳችሁን ቀጥሉ::**

2ኛ ሳሙ. 18:33:: (ዳዊት ሊገድለው ይቃጣ የነበረውን አቤሴሎምን መውደድ አልተሳነውም:: መሞቱን በተረዳ ጊዜም አለቀሰ::) «ንጉሡም እጅግ አዘነ፤ በቅጽር በሩ ዐናት ላይ ወዳለችው ቤት ወጥቶ አለቀሰ፤ ሲሄድም፤ «ልጄ አቤሴሎም ሆይ! ልጄ አቤሴሎም! በአንተ ፈንታ ምነው እኔ በሞትሁ ኖሮ! አቤሴሎም ሆይ፣ ልጄን፣ ወየው ልጄን፣» ይል ነበር::»



# ድብልቅ ጋብቻ

**1. ከማያምኑ ጋር አትጠመዱ::**

2ኛ ቆሮ. 6:14-16:: «ከማያምኑ ሰዎች ጋር አግባብ ባልሆነ መንገድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዐመፅ ጋር ምን ግንኙነት አለው? ብርሃንስ ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር ምን ስምምነት አለው? የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ኅብረት አለው? የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖት ጋር ምን ስምምነት አለው? እኛ ኮ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነን፤ እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል ተናግሮአል፤ «ከእነርሱ ጋር እኖራለሁ፣ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፤ አምላካቸውም እሆናለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ::»

**2. ካልተስማሙ በቀር ሁለት ሰዎች በአንድ መንገድ አይሄዱም::**

አሞጽ 3:3:: «በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ፣ አብረው መጓዝ ይችላሉን?»

**3. ከጥፋት ውኃ በፊት በተደረገው ድብልቅ ጋብቻ መጥፎ ውጤቶች ተከስተዋል::**

ዘፍ. 6:1-4::

**4. የእግዚአብሔር ሰዎች ወደ ድብልቅ ጋብቻ እንዳይሄዱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል፤ አማኝ ያልሆኑ ሰዎች ወደ ኃጢአት ይመሯቸዋል::**

ዘፀ. 34:16:: «ለወንዶች ልጆችህም ሴቶች ልጆቻቸውን ስታጭላቸውና እነዚህም ሴቶች ልጆች አምላኮቻቸውን በመከተል ሲያመነዝሩ፣ ወንዶች ልጆችህን ተመሳሳይ ድርጊት እንዲፈጽሙ ያነሣሡአቸዋል::

ዘዳ. 7:3-4:: «ከእነርሱ ጋር ጋብቻ አታድርግ፤ ሴት ልጆችህን ለወንድ ልጆቻቸው አትስጥ፤ ወይም ለወንድ ልጆችህ ሴት ልጆቻቸው አታምጣ፤ ምክንያቱም እኔን ከመከተል ልጆችህን መልሰው ሌሎችን አማልክት እንዲያመልኩ ስለሚያደርጉና ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር (ያህዌ) ቍጣ በላይህ ነዶ፣ ፈጥኖ ስለሚያጠፋህ ነው::»

5. እግዚአብሔር፣ ሕዝቦቹ የማያምኑ ሰዎችን ካገቡና ቢያገቡ፣ ቁጣውን ይገልጣል፡፡

ኢያሱ 23:12-13፡፡ «ነገር ግን ከእርሱ ተመልሳችሁ ተርፈው በመካከላችሁ ከሚገኙት ከእነዚህ ሕዝቦች ጋር ብትተባበሩ፣ በጋብቻም ብትተሳሰሩና ብትቀላቀሉ፣ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከእንግዲህ ከፊታችሁ እንደሚያወጣቸው ይህን ልታውቁ ይገባል፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ከዚህች መልካም ምድር እስክትጠፉ ድረስም ወጥመድና አሽክላ፣ ለጀርባችሁ ጅራፍ፣ ለዓይኖቻችሁም እሾህ ይሆኑባችኋል፡፡

6. በዕዝራ ዘመን ብዙዎች ድብልቅ ጋብቻን ፈጸሙ፡፡ ይህም ወደ በርካታ ኃጢአቶች መራቸው፣ ዕዝራም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአት ተናዘዘ፡፡

*ዕዝራ 9:1-15፡፡*

*ዕዝራ* 9:1-2፡፡ «እነዚህ ነገሮች ከተፈጸሙ በኋላ መሪዎቹ ወደ እኔ መጥተው እንዲህ አሉኝ፤ «ካህናቱንና ሌዋውያኑን ጨምሮ የእስራኤል ሕዝብ ከጎረቤቶቻቸው ከከነዓናውያን፣ ከኬጢያውያን፣ ከፌርዛውያን፣ ከኢያቡሳውያን፣ ከአሞናውያን ርኩሰት ራሳቸውን አልለዩም፡፡ ሴቶቻቸውን ለራሳቸውና ለልጆቻቸው ሚስት አድርገው ወስደዋል፤ የተቀደሰውንም ዘር ከምድር ሕዝቦች ጋር ደባልቀዋል፤ በዚህም በደል ዋነኛ የሆኑትም መሪዎችና ሹማምንቱ ናቸው፡፡»

7. የይሁዳ ሰዎች በድርብ ጋብቻ ተጠመዱ፣ ከዚህም የተነሣ ወደ ጥልቅ ኃጢአት ተመሩ፡፡ እግዚአብሔርም አዝኖባቸው ነበር፡፡

ነህ. 13:23-27፡፡ «በእነዚያም ቀናት የአሽዶድን፣ የአሞንንና የሞዓብን ሴቶች ያገቡ አይሁድ አገኘሁ፡፡ ከልጆቻቸውም እኩሌቶቹ የአሽዶድን፣ ወይም ከሌሎቹ ሕዝቦች የአንዱን ቋንቋ መናገር አይችሉም ነበር፡፡ እኔም ገሠጽኋቸው፤ ርግማንም አወረድሁባቸው፡፡ አንዳንዶቹን መታኋቸው፤ ጠጕራቸውንም ነጨሁ፡፡ በእግዚአብሔር ስም እንዲህ ስል አማልኋቸው፤ «ሴቶች ልጆቻችሁን ለወንዶች ልጆቻቸው አትስጡ፤ ሴቶች ልጆቻቸውንም ለወንዶች ልጆቻችሁ አትውሰዱ፡፡ የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን ኃጢአት የሠራው እንዲህ



ከመሰለው ጋብቻ የተነሣ አይደለምን? በብዙ መንግሥታት መካከል እንደ እርሱ ያለ ንጉሥ አልነበረም፤ በአምላኩም የተወደደ ነበረ፤ እግዚአብሔርም በእስራኤል ሁሉ ላይ ንጉሥ አደረገው፡፡ ነገር ግን ባዕዳን ሴቶች ወደ ኀጢአት መሩት፡፡ እናንተም ደግሞ ባዕዳን ሴቶችን በማግባት ይህን የመሰለ ታላቅ በደል እንደምትፈጽሙና ለአምላካችንም ታማኞች እንዳልሆናችሁ መስማት ይገባናልን?

# መታዘዝ፣ ትእዛዛትን መጠበቅ

**1. ኢየሱስ መታዘዝን ይጠብቃል::**

ዮሐ. 14:15:: «ብትወዱኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ::

**2. የኢየሱስን ትእዛዛት መጠበቅ ደስታን ያመጣል፤ በፍቅሩም ትኖራላችሁ::**

ዮሐ. 15:10-17::

**3. ወደ ሕይወት በምትመራው በቀጥተኛዋና በጠባቧ መንገድ ላይ ጽኑ፤ ሰፊው መንገድ ወደ ሞት ይመራል::**

ማቴ. 7:13-14:: «በጠባቡ በር ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው መንገድ ትልቅ፣ በሩም ሰፊ ነውና፤ ብዙዎችም በዚያ ይገባሉ:: ወደ ሕይወት የሚያደርሰው ግን መንገዱ ቀጭን፣ በሩም ጠባብ ነው፤ የሚገቡበትም ጥቂቶች ብቻ ናቸው::»

**4. «ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ» የሚል ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም::**

ማቴ. 7:21:: «በሰማይ ያለውን ያባቴን ፈቃድ ሳይፈጽም <ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤> የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም::»

**5. ኢየሱስ የጠቢቡንና የሞኙን ቤተ ሠሪዎች ምሳሌ ነገረን::**

ማቴ. 7:24-27::

**6. እግዚአብሔር መታዘዝን ይሸልማል::**

ምሳ. 13:13:: «ምክርን የሚያቃልል በራሱ ላይ ጥፋት ያመጣል፤ ትእዛዝን የሚያከብር ግን ወሮታን ይቀበላል::»

**7. መታዘዝ ከመሥዋዕት ይበልጣል::**

1ኛ ሳሙ. 15:22-23:: «ሳሙኤልም እንዲህ አለ፤ «ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ደስ የሚለውን ያህል፣ እግዚአብሔር፣ በሚቃጠል ቍርባንና መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ! መታዘዝ ከመሥዋዕት፣ ማዳመጥም ከአውራ በግ ስብ



ይበልጣል:: ዐመፅ እንደ ጥንቈላ ያለ ኀጢአት፣ እልኸኝነትም እንደ ጣዖት አምልኮ ያለ ክፉ ነገር ነው፤ አንተ የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ናቅህ፣ እርሱም ንጉሥ እንዳትሆን ንቆሃል::»

**8. የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፣ የሚለውንም አድርጉ::**

ሉቃ. 11:28:: «እርሱ ግን፣ «ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚታዘዙት ናቸው» አለ::

ያዕቆብ 1:22-25፤ 2:14-26::

**9. እግዚአብሔርን መውደድ ትእዛዛቱን መጠበቅ ነው::**

1ኛ ዮሐ. 5:2-3:: «እግዚአብሔርን ስንወድና ትእዛዛቱን ስንፈጽም የእግዚአብሔርን ልጆች እንደምንወድ በዚህ እናውቃለን፤ እግዚአብሔርን መውደድ ትእዛዛቱን መፈጸምና ነውና:: ትእዛዛቱም ከባድ አይደሉም፤

**10. የእግዚአብሔር በረከትና ሞገስ በሚታዘዙት ላይ ያርፋል፤ መታዘዝ የደስታና የሰላም መንገድ ነው::**

መዝ. 1::

መዝ. 19:7-14::

መዝ. 119: 1-8::

**11. በእውነተኝነት ጌታን ብታውቁትና ብትወድዱት፣ ፈቃዱን ለማድረግ ትፈልጋላችሁ::**

1ኛ ዮሐ. 2:3-6:: «ትእዛዛቱን ብንፈጽም እርሱን ማወቃችንን በዚህ እርግጠኞች እንሆናለን:: «እርሱን ዐውቃለሁ» እያለ ትእዛዙን የማይፈጽም ግን ሐሰተኛ ነው፤ እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም:: ነገር ግን ማንም ቃሉን ቢጠብቅ፣ በእውነት የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ ፍጹም ሆኖአል:: በእርሱ መሆናችንን የምናውቀው በዚህ ነው፤ ማንም በእርሱ እኖራለሁ የሚል፤ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል::»

1ኛ ዮሐ. 5:2-4:: «እግዚአብሔርን ስንወድና ትእዛዛቱን ስንፈጽም የእግዚአብሔርን ልጆች እንደምንወድ በዚህ እናውቃለን፤

እግዚአብሔርን መውደድ ትእዛዛቱን መፈጸም ነውና:: ትእዛዛቱም ከባድ አይደሉም፣ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል:: ዓለምን የሚያሸንፈውም እምነታችን ነው::»

2ኛ ዮሐ. 6:: «ይህም ፍቅር፣ በትእዛዛቱ መሠረት እንመላለስ ዘንድ ነው:: ትእዛዛቱም ከመጀመሪያ እንደ ሰማችሁት በፍቅር እንድትኖሩ ነው::»

12. እግዚአብሔር፣ የምትሄዱበትን መንገድ፣ ለእናንተ የተሻለውንና የሰላምን መንገድ ያስተምራችኋል::

ኢሳ. 48:17-19:: «የተቤዠህ፣ የእስራኤል ቅዱስ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ «እኔ እግዚአብሔር አምላክህ፣ የሚበጅህ ምን እንደ ሆነ የማስተምርህ፣ መሄድ በሚገባህ መንገድ የምመራህ ነኝ:: ትእዛዜን ሰምተህ ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ ሰላምህ እንደ ወንዝ፣ ጽድቅህም እንደ ባሕር ሞገድ በሆነ ነበር:: ዘርህ እንደ አሸዋ፣ ልጆችህ ስፍር እንደሌለው ትቢያ በሆኑ ነበር፤ ስማቸው አይወገድም፤ ከፊቴም አይጠፋም::»

13. የእግዚአብሔር ተስፋዎች የንጽህናንና የቅድስናን ሕይወት እንድንኖር ሊያነሣሡን ይገባል::

2ኛ ቆሮ. 7:1:: «እንግዲህ፣ ወዳጆች ሆይ፤ ይህ የተስፋ ቃል ስላለን፣ ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን እናንጻ፤ እግዚአብሔርንም በመፍራት ቅድስናችንን ፍጹም እናድርገው::»

14. በክርስቶስ የተሰጣችሁ ነጻነት ክፋትን ለማድረግ ሳይሆን እርሱን ለማገልገል ተጠቀሙበት::

ገላ. 5:13:: «ወንድሞቼ ሆይ፤ ነጻ እንድትሆኑ ተጠርታችኋል፤ ነጻነታችሁን ግን ሥጋዊ ምኞታችሁን መፈጸሚያ አታድርጉት፤ ይልቁንም አንዱ ሌላውን በፍቅር ያገልግል::»

15. ከመታዘዝ መንገድ ወደ ግራም ሆነ ወደ ቀኝ ፈቀቅ አትበል::

ምሳ. 4:25-27:: «ዐይኖችህ በቀጥታ ይመልከቱ፤ ትክ ብለህም ፊት ለፊት እይ:: የእግርህን ጐዳና አስተካክል፤ የጸናውን መንገድ ብቻ ያዝ:: ወደ ቀኝ ወደ ግራ አትበል፤ እግርህን ከክፉ ጠብቅ::»



# ክፋን ማሸነፍ

## (ሌሎች ቢበድሉህ ምን ማድረግ እንዳለብህ)

1. ከበደለህ ሰው ጋር በግል ለመግባባት ጥረት አድርግ::

ማቴ. 18:15:: «ወንድምህ ቢበድልህ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻ ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው:: ቢሰማህ፣ ወንድምህን እንደ ገና የራስህ ታደርገዋለህ::»

2. ችግሩ ባይፈታ አንድ ወይም ሁለት ሰዎችን ከአንተ ጋር ውሰድ::

ማቴ. 18:16:: «ባይሰማህ ግን ቃል ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ፊት ስለሚጸና፣ አንድ ወይም ሁለት ሰው ይዘህ አነጋግረው::»

3. ያም ካልሠራ ጉዳዩን ለቤተ ክርስቲያን ተናገር እርዳታን ከዚያ ፈልግ::

ማቴ. 18:17:: «እርሱን ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገር፤ ቤተ ክርስቲያንንም ባይሰማ እንደ አሕዛብና እንደ ቀረጥ ሰብሳቢ ቍጠረው::»

4. የሚያሳድዷችሁን መርቁ::

ሮሜ 12:14:: «የሚያሳድዷችሁን መርቁ፤ መርቁ እንጂ አትርገሙ::»

5. ጳውሎስ ክፋን እንዴት ማሸነፍ እንደሚገባና አንድ ሰው ሲበድላችሁ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ይናገራል::

ሮሜ 12:17-21::

6. በቀልን አትፈልጉ

ሮሜ 12:17:: «ለማንም ክፉን በክፉ አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት በጎ የሆነውን ነገር ለማድረግ ትጉ::»

ሮሜ 12:19:: «ወዳጆቼ ሆይ፤ ለእግዚአብሔር ቍጣ ፈንታ ስጡ እንጂ አትበቀሉ፤ «በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ» ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና::»

ምሳ. 20:22:: «ለደረሰብኝ በደል ብድሬን ባልመልስ!» አትበል፤ እግዚአብሔርን ጠብቅ፤ እርሱ ይታደግሃል::

7. ከሰዎች ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ::

ሮሜ 12:18:: «ቢቻላችሁስ በበኩላችሁ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ::»

8. ክፉን በመልካም አሸንፍ::

ሮሜ 12:21:: «ክፉን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ::

9. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ በግፍ መከራን በመቀበል ኢየሱስን ምሰል፤ ከዚያ በተለየ መልኩ አትሞክረው::

1ኛ ጴጥ. 2:18-23::

1ኛ ጴጥ 2:19-23:: «ስለ እግዚአብሔር ሲል የግፍ መከራን የሚቀበል ሰው ምስጋናን ያገኛል:: ክፉ ሥራ ሠርታችሁ ብትቀጡና ብትታገሡ ምን ምስጋና ይኖራችኋል? ነገር ግን መልካም ሥራ ሠርታችሁ መከራ ብትቀበሉና ብትታገሡ ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ ›‹ስጋና ያስገኝላችኋል:: የተጠራችሁትም ለዚሁ ነው፤ ምክንያቱም ክርስቶስ ስለ እናንተ መከራን የተቀበለው የእርሱን ፈለግ እንድትከተሉ ምሳሌን ሊተውላችሁ ነው:: «እርሱ ኀጢአት አላደረገም፤ በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም::» ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፤ መከራ ሲደርስበት አልዛተም፤ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ::»

1ኛ ጴጥ. 3:8-9:: «በመጨረሻም ሁላችሁ በአንድ ሐሳብ ተስማሙ፤ እርስ በርሳችሁ ተሳሰቡ፤ እንደ ወንድማማቾች ተዋደዱ፤ ርኅሩኆችና ትሑታን ሁኑ:: ክፉን በክፉ ወይም ስድብን በስድብ ፈንታ አትመልሱ፤ በዚህ ፈንታ ባርኩ፤ ምክንያቱም እናንተ የተጠራችሁት እንደዚህ ያሉትን ነገሮች እያደረጋችሁ በረከትን ለመውረስ ነው::»

10. ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ መልካምም አድርጉላቸው::

ማቴ. 5:43-47::



ሮሜ 12:20:: «ይልቁንስ፣ «ጠላትህ ቢራብ አብላው፤ ቢጠማም አጠጣው:: ይህን በማድረግህም የእሳት ፍም በራሱ ላይ ትከምራለህ::»

11. ሌላውን ጉንጭህን አዙርለት፤ ለበደለህ ሰው ደግ ሁንለት::

ማቴ. 5:38-42::

1ኛ ተሰ. 5:15:: «ማንም በክፉ ፈንታ ክፉ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፤ ነገር ግን እርስ በርሳችሁም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ሁልጊዜ መልካም የሆነውን ነገር ለማድረግ ተጣጣሩ::»

12. በባልንጀራህ ላይ በክፉ አትመስክር፣ አትበቀለውም::

ምሳ. 24:28-29:: በባልንጀራህ ላይ ያለ ምክንያት አትመስክር፤ በከንፈርህም አትሸንግል:: «በእኔ ላይ እንደ ሠራብኝ እሠራለታለሁ፤ ስለ አድራጎቱም የእጁን እመልስለታለሁ» አትበል::

13. ሙሴ አንድ ሰው ከበደላችሁ በኋላ ማድረግ የሚገባችሁን ተግባራዊ ጉዳዮች አስቀምጧል::

ዘፀ. 23: 4-5:: «የጠላትህ በሬ ወይም አህያ ሲባዝን ብታገኘው ወደ እርሱ መልሰው:: የሚጠላህ ሰው አህያ፣ ጭነት ከብዶት ወድቆ ብታየው ርዳው እንጂ ትተኸው አትሂድ::»

## ኃጢአትን ማሸነፍ፣ መለወጥ
## (እግዚአብሔርን ለማስደሰትና ችግሮችን ለማቃለል)

በተጨማሪ እድገታዊ ቅድስናን በገጽ 170 ላይ፣ እንዲሁም ንስሐን በገጽ 186 ላይ ተመልከቱ።

1. **እውነተኛ ክርስቲያኖች መለወጥ ይችላሉ፣ ምክንያቱም በመንፈሳዊ ተሐድሶ በኩል እግዚአብሔር የሚቻል አድርጐታል።**

2ኛ ቆሮ. 5:17። «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፣ እነሆ አዲስ ሆኖአል።»

ሕዝ. 36:25-27። «ንጹሕ ውሃ እረጫችኋለሁ፤ እናንተም ንጹሐ ትሆናላችሁ፤ ከርኵሰታችሁ ሁሉና ከጣዖታቶቻችሁ ሁሉ አነጻችኋለሁ። አዲስ ልብ እሰጣችኋለሁ፤ አዲስ መንፈስም በውስጣችሁ አሳድራለሁ፤ የድንጋይ ልባችሁን ከእናንተ አስወግዳለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ። መንፈሴን በውስጣችሁ አሳድራለሁ፤ ሥርዐቴን እንድትከተሉና ሕጌን በጥንቃቄ እንድትጠብቁ አደርጋለሁ።»

2. **አማኞች የእግዚአብሔር ልጆችና፣ በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ የተወለዱ ናቸው።**

ዮሐ. 1:12-13። «ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው። እነዚህም በእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ፣ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።»

ቲቶ 3:4-6። «ነገር ግን የአዳኛችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር በተገለጠ ጊዜ፣ ስላደረግነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን፣ ከምሕረቱ የተነሣ አዳነን። ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው፤ ይህንም መንፈስ እግዚአብሔር በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእኛ ላይ አትረፍርፎ አፈሰሰው።»

3. **ሁሉም ክርስቲያኖች በእኛ ውስጥ በሚኖረውና ኃጢአትን ለማሸነፍና መንፈሳዊ ሕይወት ለመምራት ኃይል በሚሰጠው በመንፈስ ቅዱስ እንዲኖሩ ተጠርተዋል።**



ሮሜ 8:1-14።

ሮሜ 8:9። «እናንተ ግን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ፣ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ናችሁ። ማንም የክርስቶስ መንፈስ ካለው፣ እርሱ የክርስቶስ አይደለም።»

ሮሜ 8:13-14። «እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞታላችሁና፤ ክፉ የሆነውን የሥጋ ሥራ በመንፈስ ብትገድሉ ግን፣ በሕይወት ትኖራላችሁ፤ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።»

4. **እግዚአብሔር በሁሉም የሕይወታችን አቅጣጫዎች ዙሪያ ደኅንነታችንን እንድንፈጽም ይጠራናል። በራሳችን ልንራመድ አያስፈልገንም።**

ፊል. 2:12-13። «ስለዚህ፣ ወዳጆቼ ሆይ፤ ሁልጊዜም ታዛዦች እንደ ነበራችሁ ሁሉ፣ አሁንም እኔ በአጠገባችሁ ሳለሁ ብቻ ሳይሆን፣ ይልቁንም አሁን በሌለሁበት ጊዜ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ እንደ በጎ ፈቃዱ መፈለግንና ማድረግን በእናንተ ውስጥ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።»

5. **እግዚአብሔር ለሕይወትና ለመንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ ሰጥቶናል።**

2ኛ ጴጥ. 1:3። «በገዛ ክብሩና በጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኀይል ሰጥቶናል።»

6. **እግዚአብሔር የሚያስቸግራችሁን ያን ልዩ ኃጢአት አሸንፋችሁ ፈቃዱን ማድረግ ትችሉ ዘንድ ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል።**

2ኛ ቆሮ. 9:8። «ሁልጊዜ በሁሉ ነገር የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ ሁሉ እንድትተርፉ፣ እግዚአብሔር ጸጋን

ሊያበዛላችሁ ይችላል::»

7. እውነተኛ ክርስቲያን በኃጢአት መኖርን አይቀጥልም::

1ኛ ዮሐ. 3:4-10::

1ኛ ዮሐ. 3:6:: «በእርሱም የሚኖር ኀጢአትን አያደርግም፤ ኀጢአት የሚያደርግ ግን እርሱን አላየውም ወይም አላወቀውም::»

1ኛ ዮሐ. 3:9:: ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኀጢአትን አያደርግም፤ የእርሱ ዘር በውስጡ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደም ኀጢአትን ሊያደርግ አይችልም::»

8. በተፈጥሮአችን የኃጢአት ባሪያዎች ነን:: ክርስቶስ ነፃ ሊያወጣን መጣ::

ዮሐ. 8:31-36::

ዮሐ. 8:34-36:: «ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «እውነት እላችኋለሁ፤ ኀጢአት የሚያደርግ የ ኃጢአት ባሪያ ነው፤ ባሪያ ለዘለቄታ በቤተሰቡ ውስጥ አይኖርም፤ ልጅ ግን ምን ጊዜም በቤት ይኖራል:: እንግዲህ ወልድ ነፃ ካወጣችሁ፣ በእውነት ነጻ ትሆናላችሁ::»

9. ክርስቲያኖች የጽድቅ ባሪያዎች ይሆኑ ዘንድ ነጻ ሆነዋል::

ሮሜ 6:15-18:: «እንግዲህ ምን ይሁን? ከሕግ በታች ሳይሆን፣ ከጸጋ በታች በመሆናችን ኀጢአት እንሥራን? በጭራሽ አይገባም! ራሳችሁን እንደ ባሪያ አድርጋችሁ ስታቀርቡ፣ ለምትታዘዙት ለእርሱ፣ ይኸውም ወደ ሞት ለሚወስደው ለኀጢአት ወይም ወደ ጽድቅ ለሚያደርሰው ለመታዘዝ ባሮች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? ነገር ግን የኀጢአት ባሮች የነበራችሁ ቢሆንም፣ ለተሰጣችሁለት ትምህርት በሙሉ ልብ የታዘዛችሁ በመሆናችሁ፣ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፤ ከኀጢአት ነጻ ወጥታችሁ፣ የጽድቅ ባሪያዎች ሆናችኋል::»

10. ኃጢአትን ለማሸነፍና ሰውነታችን ጌታን ብቻ እንዲያገለግል



ለማድረግ ጠንክረን መሥራታችንን መቀጠል አለብን::

ሮሜ 6:19-23::

11. ለእግዚአብሔር አዳኝ ጸጋ ምላሽ ትሰጡ ዘንድ አሮጌውን ኃጢአተኛ መንገዳችሁን ማስወገድና አዲሱንና መንፈሳዊውን መንገድ መለማመዳችሁን መቀጠል ያስፈልጋችኋል::

ኤፌ. 4:22-24:: «ቀድሞ ስለነበራችሁበት ሕይወትም፣ በሚያታልል ምኞቱ የጎደፈውን አሮጌ ሰውነታችሁን አውልቃችሁ እንድትጥሉ ተምራችኋል፤ ደግሞም በአእምሮአችሁ መንፈስ እንድትታደሱ፣ እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው::

12. ሐዋርያው ጳውሎስ ምን መደረግ እንዳለበት ውስን የሆኑ ትምህርቶችን ይሰጠናል::

ኤፌ. 4:25-5:21::

ቆላ. 3:1-17::

13. እና በመንፈስ እንድንመላለስ፣ ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችንን እንድናስወግድና የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ እንድንሻ ታዝዘናል::

ገላ. 5:16-26::

ገላ. 5:19-26:: «የሥጋ ሥራ ግልጽ ነው:- ይኸውም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናት፣ ቍጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኛነት፣ ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ እንዲሁም እነዚህን የመሰለው ነው:: አስቀድሜ እንዳልሁ፣ አሁንም አስጠነቅቃችኋለሁ፤ በእንዲህ ሁኔታ የሚኖሩ ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም:: የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው:: እንደዚህ ያሉትንም የሚከለክል ሕግ የለም:: የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋር ሰቅለውታል:: በመንፈስ የምንኖር ከሆን፣ በመንፈስ እንመላለስ :: እርስ በርሳችን

እየተጎንታተልንና እየተቀናናን በከንቱ ውዳሴ እንመካ::»

14. አመንዝሮች፣ ሰካራሞች፣ ግብረ ሰዶማውያን በዚህም ምክንያት ፊውስ በሌለው በሽታ የተመቱ ብዙዎች በእግዚአብሔር ኃይልና ጸጋ ኃጢአታቸውን ማሸነፍ ይችላሉ::

1ኛ ቆሮ. 6:9-11:: «ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ አታውቁምን? በዚህ ነገር አትታለሉ፤ ሴሰኞች፤ ጣዖት አምላኪዎች፣ አመንዝሮች፣ ወንደቃዎች፣ ግብረ ሰዶማውያን፣ ወይም ሌቦች፣ ስግብግቦች፣ ሰካራሞች፣ ተሳዳቢዎችና ቀማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም:: ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና፣ በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል::

15. በማናቸውም ኃጢአቶች ቁጥጥር ሥር እንድትሆኑ አትፍቀዱ::

1ኛ ቆሮ. 6:12:: «ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል፤» ይሁን እንጂ ሁሉም ነገር አይጠቅምም፤ «ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል፤» ይሁን እንጂ ምንም ነገር በእኔ ላይ አይሠለጥንም::»

2ኛ ጴጥ. 2:19:: «እነርሱ ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሆነው ሳሉ፣ ሌሎችን ነጻ ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጧቸዋል፤ ሰው ለተገዛለት ለዚያ ነገር ባሪያ ነውና::»

16. መንፈሳዊ ውጊያን ስታደርጉ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ በሙሉ ተጠቀሙ::

ኤፌ. 6:10-18::

ኤፌ. 6:10-11:: «በተረፈ በጌታና ብርቱ በሆነው ኀይሉ ጠንክሩ:: የዲያብሎስን የተንኰል ሥራ መቋቋም ትችሉ ዘንድ፣ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ ልበሱ::»

17. ንቁ! ባላጋራችሁ ዲያብሎስ፣ ሊውጣችሁ ይፈልጋል::

1ኛ ጴጥ. 5:8-9:: «ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፣ ንቁም፤ ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሣ አንበሳ ወዲያ ወዲህ ይዞራል:: በዓለም ዙሪያ ያሉት ወንድሞቻችሁ



ተመሳሳይ መከራ እንደሚቀበሉ ዐውቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት::

18. የኃጢአት ባሪያዎች ሆናችሁ እንድትኖሩ የሚፈልገውን ሰይጣንን ተቃወሙት::

ያዕ. 4:7:: እንግዲህ መልካም የሆነውን ነገር ማድረግ እንዳለበት እያወቀ የማያደርግ ሰው ኀጢአት ያደርጋል::

19. ሰይጣን ሊያስናክላችሁ ሌሎች ሰዎችን ሊጠቀም ይችላል:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ ወይም ከሆነ ፈጽማችሁ አትስሙ::

ምሳ. 1: 10-19::

ምሳ. 1:10:: «ልጄ ሆይ፤ ኀጢአተኞች ቢያባብሉህ፣ እሺ አትበላቸው::»

20. ጸንታችሁ ቁሙ፤ አትወላውሉ፣ አትነቃነቁ::

1ኛ ቆሮ. 15:58:: «ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ጸንታችሁ ቁሙ፤ በምንም ነገር አትናወጡ:: ለጌታ ሥራ ዘወትር ይምትተጉ ሁኑ፤ ምክንያቱም ለጌታ የምትደክሙት በከንቱ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ::»

21. ተግታችሁ የክፋትን መንገድ አስወግዱ፣ ከእርሱ ተመለሱ::

ምሳ. 4:14-15:: «ወደ ኀጥኣን ጐዳና እግርህን አታንሣ፤ በክፉ ሰዎች መንገድ አትሂድ፤ ከዚያ አትድረስ፤ አትጓዝበት፤ ሽሽው፤ መንገድህን ይዘህ ሂድ::»

22. ዘማሪው እንዳደረገው በኀጢአተኛ አስተሳሰቦች፣ ቃላትና ተግባራት ላይ ድልን እንዲሰጣችሁ ወደ እግዚአብሔር በትጋትና ልብን በሚነካ መንገድ ጸልዩ::

ምሳ. 19:12-14:: «የንጉሥ ቍጣ እንደ አንበሳ ግሣት ነው፤ በፊቱ ሞገስ ማግኘትም በሣር ላይ እንዳለ ጠል ነው:: ተላላ ልጅ ለአባቱ መጥፊያ ነው፤ ጨቅጫቃ ሚስትም እንደማያቋርጥ ጠፈጠፍ ናት:: ቤትና ሀብት ከወላጆች ይወረሳሉ፤ አስተዋይ ሚስት ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ናት::»

ለተጨማሪ መረጃ እድገታዊ ቅድስናን በገጽ 170 ላይ ተመልከቱ::

# ሰላም፣ እረፍት

በተጨማሪ ጎሊናን በገጽ 55 ላይ ተመልከቱ::

1. ክርስቶስ ወደ እርሱ በእምነት ለቀረቡ ሁሉ ሰላምና እረፍት ይሰጣል::

ማቴ. 11:28-30:: «እናንተ ሸክም የከበዳችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም ዕረፍት እሰጣችኋለሁ:: ቀንበሬን ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ በልቤ የዋህና ትሑት ነኝና፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና::»

2. ሰላም በክርስቶስ ላይ ባለን እምነት አማካይነት ከምናገኘው የደኅንነት ቅድስና ይመጣል::

ሮሜ 5:1:: እንግዲህ በእምነት ስለ ጸደቅን፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን::

3. ኢየሱስ ሰላምን ይሰጠናል::

ዮሐ. 14:27:: «ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጣችሁ አይደለም:: ልባችሁ አይጨነቅ፤ አይፍራም::»

4. እኛ ሰላም ይኖረን ዘንድ ኢየሱስ ስለ እኛ ኃጢአት ተቀጣ::

ኢሳ. 53:5:: «ነገር ግን እርሱ ስለ መተላለፋችን ተወጋ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን::»

5. በኢየሱስ እግር ላይ በማልቀስ የተጸጸተችው ሴት በእርሱ በኩል ሰላምን አገኘች::

ሉቃ. 7:36-50::

ሉቃ. 7:48:: «ኢየሱስም ሴቲቱን፣ «ኃጢአትሽ ተሰርዮልሻል» አላት::»

ሉቃ. 7:50:: «ኢየሱስም ሴቲቱን፣ «እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ« አላት::»

6. በጌታ ላይ የሆነ የትሕትና መታመን ሰላምን ያመጣል::



መዝ. 4:8:: በሰላም እተኛለሁ፤ አንቀላፋለሁም፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ያለ ሥጋት የምታሳድረኝ አንተ ብቻ ነህና::

7. እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰላምን ተስፋ ይሰጣል::

መዝ. 85:8:: እግዚአብሔር አምላክ የሚናገረውን እሰማለሁ፤ ለሕዝቡ፣ ለቅዱሳኑ ሰላምን ይናገራልና፤ ዳሩ ግን ወደ ከንቱ ምግባራቸው አይመለሱ::

8. ሰላም በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር የመሆን ውጤት ነው::

ሮሜ 8:6:: የሥጋን ነገር ማሰብ ሞት ነው፤ የመንፈስን ነገር ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው::

9. ሰላም የመንፈስ ፍሬ ነው::

ገላ. 5:22-23:: የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት ራስን መግዛት ነው::

10. እግዚአብሔር አእምሮአቸውን በእርሱ ላይ ላደረጉ ሰዎች ሰላምን ይሰጣል::

ኢሳ. 26:3-4:: በአንተ ላይ ታምናለችና፣ በአንተ የምትደገፈውን ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ:: በእግዚአብሔር ለዘላለም ታመኑ፤ ጌታ እግዚአብሔር የዘላለም ዐምባ ነውና::

11. የእግዚአብሔር ሰላም በእምነት በመጸለይ ይመጣል::

ፊል. 4:6-7:: በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ፣ ከምስጋናም ጋር ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ እንጂ ስለ ማንኛውም ነገር አትጨነቁ:: ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሰላም፣ ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል::

12. ኢየሱስ የሰላም አለቃ ነው::

ኢሳ. 9:6:: ሕፃን ተወልዶልናልና፤ ወንድ ልጅ ተሰጥቶናል፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል:: ስሙም፣ ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም ልዑል ይባላል::

13. በቅንነት የሚሄዱ ወደ ሰላም ውስጥ ይገባሉ::

ኢሳ. 57:2:: በቅንነት የሚሄዱ፣ ሰላም ይሆንላቸዋል፤

መኻታቸው ላይ ያርፋሉ።

14. እግዚአብሔር የተሰበሩ ሰዎችን ያነቃቃል፣ ይፈውሳል፣ ሰላምም ይሰጣቸዋል።

ኢሳ. 57፡14-21

ኢሳ. 57፡19-20። «በእስራኤል አልቃሾች ከንፈር ላይ ምስጋና እፈጥራለሁ። በቅርብና በሩቅ ላሉት ሰላም ይሁን፣ እኔ እፈውሳቸዋለሁ» ይላል እግዚአብሔር። ክፉዎች ግን ማዕበሉ ጭቃና ጉድፍ እንደሚያወጣ፣ ጸጥ ማለት እንደማይችል፣ እንደሚናወጥ ባሕር ናቸው።

15. ለክፉዎች ሰላም የላቸውም

ኢሳ. 57፡21። አምላኬ፣ «ለክፉዎች ሰላም የላቸውም» ይላል።

16. ሐሰተኛ ነቢያት ሰላም ሳይኖር፣ «ሰላም ሰላም» ይላሉ።

ኤር. 8፡11-12። «የሕዝቤ ቍስል ብርቱ እንዳይደለ በመቍጠር፣ የተሟላ ፈውስ ሳይኖር እንዲሁ ያክማሉ፤ ሰላም ሳይኖር፣ «ሰላም፣ ሰላም» ይላሉ። ርኩሰት ሲፈጽሙ ዐፍረው ነበርን? የለም! በጭራሽ አላፈሩም፤ ኀፍረት ምን እንደሆነም አያውቁም። ስለዚህ ከወደቁት ጋር ይወድቃሉ፤ በምቀጣቸው ጊዜ ይዋረዳሉ» ይላል እግዚአብሔር።



# አስታራቂዎች፣ ሰላም ጠባቂዎች

በተጨማሪ ሌሎችን ይቅር ማለት የሚለውን በገጽ 99 ላይ ተመልከቱ።

ማስታወሻ፡- ስለ አስታራቂነት፣ ጸጥታ ጠባቂነት፣ ሰላም አጉልባችነት፣ ስምምነትና ኅብረት የሚናገሩ ክፍሎች ተዘርዝረዋል። በእነዚህ መመሪያዎች መሠረት መኖር ከቤትና በዘመድ አዝማድ አባላት መካከል መጀመሩ አስፈላጊ እንደሆነ ማወቅ ጠቃሚ ነው።

1. ኢየሱስ አስታራቂዎች እንደሚባረኩ አወጀ።

ማቴ. 5፡9። «ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉና።»

2. ከሰዎች ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር እንድትችሉ ከፍተኛ ጥረትና የምትችሉትን ሁሉ አድርጉ።

ዕብ. 12፡14። ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር የሚቻላችሁን ሁሉ አድርጉ፤ ለመቀደስም ፈልጉ፤ ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ማየት አይችልም።

ሮሜ 12፡18። ቢቻላችሁስ በበኩላችሁ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።

3. ክፉ ወይም ውሸት ባለመናገር ሰላምን ፈልጉ፣ ተከታተሉትም።

መዝ. 34፡13-14። አንደበትህን ከክፉ ነገር ከልክል፤ ከንፈርህንም ከሽንገላ ጠብቅ። ከክፉ ሽሽ፤ መልካሙንም አድርግ፤ ሰላምን ፈልጋት፤ ተከተላትም።

4. የእግዚአብሔር ጥበብ ሰላም ወዳድ ናት።

ያዕ. 3፡17-18። ከሰማይ የሆነችው ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፤ በኋላም ሰላም ወዳድ፣ ታጋሽ፣ እሺ ባይ፣ ምሕረትና መልካም ፍሬ የሞላባት፣ አድልዎና ግብዝነት የሌለባት ናት። የጽድቅም ፍሬ ሰላምን ለሚያደርጉ በሰላም ይዘራል።

5. ፍጹማዊነትን አልም፣ አንድ አሳብ ይኑርህ፣ በሰላም ኑር።

2ኛ ቆሮ. 13:11። «በተረፈ ወንድሞች ሆይ፤ ደኅና ሁኑ። ፍጹማን ሁኑ፤ ምክሬን ስሙ፤ አንድ ሐሳብ ይኑራችሁ፤ በሰላምም ኑሩ። የፍቅርና የሰላም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል።»

6. እግዚአብሔር ልጆቹ በአንድነት በኅብረት ሲኖሩ በማየት ይደሰታል።

*መዝ. 133:1-3።*

*መዝ.* 133:1። «ወንድሞች ተስማምተው በአንድነት ሲኖሩ፣ እንዴት መልካም ነው! ምንኛስ ደስ ያሰኛል!»

7. አንድ ሰው በአንተ ላይ አንዳች ቢኖረውና ግንኙነታችሁ ቢበላሽ ወይም ቢቋረጥ፣ ለመታረቅ የመጀመሪያው ተነሣሽ ልትሆን ያስፈልግሃል። ይህም በእሑድ ቀን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከመሆን የበለጠ አንገብጋቢ ነው።

ማቴ. 5:23-24። «ስለዚህ መባህን በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር በምታቀርብበት ጊዜ ወንድምህ የተቀየመብህ ነገር መኖሩ ትዝ ቢልህ፣ መባህን በዚያው በመሠዊያ ፊት ተወው፣ በመጀመሪያ ሄደህ ከወንድምህ ጋር ተስማማ፤ ከዚያም ተመልሰህ መባህን ለእግዚአብሔር አቅርብ።»

8. አንድ ሰው ቢበድልህ ጉዳዩን ለማስተካከልና ሰላምን ለመፍጠር ቀዳሚውን እርምጃ ወሳጁ አንተ መሆን አለብህ።

ማቴ. 18:15። «ወንድምህ ቢበድልህ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻ ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው። ቢሰማህ፣ ወንድምህን እንደ ገና የራስህ ታደርገዋለህ።»

9. ያ ሰው የማይሰማህ ከሆነ፣ የአንድ ወይም የሁለት ሌሎች አማኞችን እርዳታ ፈልግ።

ማቴ. 18:16። «ባይሰማህ ግን ቃል ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ፊት ስለሚጸና፣ አንድ ወይም ሁለት ሰው ይዘህ አነጋግረው።»

10. እነርሱን የማይሰማ ከሆነ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት።



ማቴ. 18:17። «እነርሱን ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገር፤ ቤተ ክርስቲያንንም ባይሰማ እንደ አሕዛብና እንደ ቀረጥ ሰብሳቢ ቍጠረው።»

11. ሰላምን፣ ስምምነትንና አንድነትን ለማበረታታት ስትሉ እያንዳንዳችሁ ከልብ ተዋደዱ። ብዙ ጥፋቶችንና ኃጢአቶችንም አለፉ።

1ኛ ጴጥ. 1:22-23። እንግዲህ ለእውነት በመታዘዝ ነፍሳችሁን ስላነጻችሁ፣ ለወንድሞቻችሁ ቅን ፍቅር ይኑራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም አጥብቃችሁ ከልብ ተዋደዱ። ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር ሳይሆን ሕያው በሆነና ጸንቶ በሚኖር፣ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ከማይጠፋ ዘር ነው።

1ኛ ጴጥ 4:8። ፍቅር ብዙ ኀጢአትን ይሸፍናልና ከሁሉ በላይ እርስ በርሳችሁ ከልብ ተዋደዱ።

12. ጴጥሮስ ሰላምንና ስምምነትን ልናስፋፋባቸው የምንችልባቸውን ሌሎች መንገዶች ይሰጠናል።

1ኛ ጴጥ. 3:8-11። በመጨረሻም ሁላችሁ በአንድ ሐሳብ ተስማሙ፤ እርስ በርሳችሁ ተሳሰቡ፤ እንደ ወንድማማቾች ተዋደዱ፤ ርኅሩኆችና ትሑታን ሁኑ። ክፉን በክፉ ወይም ስድብን በስድብ ፈንታ አትመልሱ፤ በዚህ ፈንታ ባርኩ፤ ምክንያቱም እናንተ የተጠራችሁት እንደነዚህ ያሉትን ነገሮች እያደረጋችሁ በረከትን ለመውረስ ነው። ስለዚህ፣ «ሕይወትን የሚወድ፣ መልካም ቀኖችን ሊያይ የሚፈልግ፣ ምላሱን ከክፉ፣ ከንፈሮቹንም ተንኰል ከመናገር ይከልክል። ከክፉ ይራቅ፤ መልካምንም ያድርግ፤ ሰላምን ይፈልግ፤ ይከተላትም።»

13. እግዚአብሔር የሰጣችሁን ነጻነት አንዳችሁ ሌላችሁን ለማገልገልና መራራ ጥላቻን ለማስወገድ ተጠቀሙበት።

ገላ. 5:13-15። ወንድሞቼ ሆይ፤ ነጻ እንድትሆኑ ተጠርታችኋል፤ ነጻነታችሁ ግን ሥጋዊ ምኞታችሁን መፈጸሚያ አታድርጉት፤ ይልቁንም አንዱ ሌላውን በፍቅር ያገልግል። ሕግ

ሁሉ በአንድ ቃል ተጠቃሉአል፤ ይኸውም፤ «ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» የሚል ነው:: ነገር ግን እርስ በርሳችሁ የምትነካከሱና የምትበላሉ ከሆነ፣ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ::

14. ሰላምንና ስምምነትን የሚያጠፉትን የኃጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራዎችን አስወግዱ::

ገላ. 5:19-20:: የሥጋ ሥራ ግልጽ ነው:- ይኸውም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናት፣ ቍጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት ፣ አድመኝነት፤...

ገላ. 5:22-23:: የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው:: እንደነዚህ ያሉትንም የሚከለክል ሕግ የለም::

15. በኢየሱስ የተሰጠውን ወርቃማ ትእዛዝ ተከተሉ::

ማቴ. 7:12:: ሌሎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ነገር እናንተም አድርጉላቸው፤ ኦሪትም፣ ነቢያትም በዚህ ይጠቃለላሉና::

16. ታገሡ:: እርስ በርስ ተሸካከሙ::

ምሳ. 15:18:: ግልፍተኛ ሰው ጠብ ያነሣሣል፤ ታጋሽ ሰው ግን ጠብን ያበርዳል::

ምሳ. 20:3:: ከጠብ መራቅ ለሰው ክብሩ ነው፤ ተላላ ሁሉ ግን ለጥል ይቸኩላል::

ምሳ. 26:21:: ከሰል ፍምን፣ ዕንጨትም እሳትን እንደሚያቀጣጥል፣ አዋኪ ሰውም ጠብን ያባብሳል::

1ኛ ቆሮ. 13:14:: ፍቅር ታጋሽ ነው፤ ደግሞም ቸር ነው:: ፍቅር አይመቀኝም፤ አይመካም፤ አይታበይም፤

17. ቁጡ ሰው ጠብን ያነሣሣል::

ምሳ. 29:22:: ቍጡ ሰው ጠብን ይጭራል፤ ግልፍተኛም ብዙ ኀጢአት ይሠራል::

18. የሌላውን ሰው ቁጣ ማነሣሣትም ጠብን ይፈጥራል::

ምሳ. 30:33:: ወተት ሲናጥ ቅቤ እንደሚወጣው፣ አፍንጫን



ሲያሹት እንደሚደማ፣ ቍጣን ማነሣሣትም ጥልን ይፈጥራል::

19. ሰላምን ሊያስፋፉ የሚችሉትን የክርስቶስን የሚመስሉ ባሕርያትን ተላበሱ::

ቈላ. 3:12-13:: እንግዲህ የተቀደሳችሁና የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ምርጦች እንደ መሆናችሁ ርኅራኄን፣ ቸርነትን፣ ትሕትናን፣ ጨዋነትንና ትዕግሥትን ልበሱ፤ እርስ በርሳችሁ ተቻቻሉ፤ ከእናንተ አንዱ በሌላው ላይ ቅር የተሰኘበት ነገር ቢኖር ይቅር ተባባሉ፤ ጌታ ይቅር እንዳላችሁ እናንተም ሌላውን ይቅር በሉ::

20. ሰላም በሞላበት ሁኔታ እግዚአብሔር የፈጠረውን ልዩነት በአንድነት ውስጥ አስተናግዱ::

ኤፌ. 4:1-16::

ኤፌ. 4:2-6:: ፍጹም ትሑታንና ገሮች ሁኑ፤ እርስ በርሳችሁም በፍቅር እየተቻቻላችሁ ትዕግሥተኞች ሁኑ:: በሰላም ማሰሪ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ:: በተጠራችሁ ጊዜ ወደ አንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ ሁሉ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ፤ ከሁሉም በላይ የሆነ፣ በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉም የሚኖር የሁሉም አባት የሆነ አንድ አምላክ አለ::

21. በአከራካሪ ጉዳዮች ላይ እርስ በርሳችሁ አትፈራረዱ::

ሮሜ 14:1-23::

ሮሜ 14:1:: በእምነቱ ደካማ የሆነውን ሰው፣ አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በአቋሙ ሳትፈርዱበት ተቀበሉት::

ሮሜ 14:19:: ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና እርስ በርሳችንም የምንተናነጽበትን ማንኛውንም ጥረት እናድርግ::

22. ሰላምን በሚያስፋፋ መንገድ ተነጋገሩ::

ኤፌ. 4:15:: ይልቁንም እውነትን በፍቅር እየተነጋገርን፣ ራስ ወደ ሆነው ወደ እርሱ በነገር ሁሉ እናድጋለን፤ እርሱም ክርስቶስ ነው::

ኤፌ. 4:29:: እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎችን የሚያንጽና ሰሚዎችን የሚጠቅም ቃል እንጂ የማይረባ ቃል ከአፋችሁ አይውጣ::

23. በአከራካሪ ጉዳዮች ላይ በብርቱ ሁኔታ የማትስማማ ቢሆንም እንኳ፣ ሌሎችን በአንድነት መንፈስ ተቀበላቸው:: ዋናው ዓላማ እግዚአብሔርን ማክበር ነው::

ሮሜ 15:5-7:: ብርታትንና መጽናናትን የሚሰጥ አምላክ፣ ክርስቶስ ኢየሱስን ስትከተሉ፣ በመካከላችሁ የአንድነትን መንፈስ ይስጣችሁ፤ ይኸውም በአንድ ልብና በአንድ አፍ ሆናችሁ፣ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክና አባት ታከብሩ ዘንድ ነው:: እንግዲህ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሆን ዘንድ ክርስቶስ እንደተቀበላችሁ፣ እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ::

24. በአንተና በሌላ ክርስቲያን መካከል የሕግ ክርክር ቢነሣ፣ ለእርዳታ ወደማያምኑ ሰዎች ዘወር አትበል:: ይልቁንም የአንድ ወይም የሁለት ክርስቲያኖችን እርዳታ ፈልግ::

1ኛ ቆሮ. 6:1-8::

1ኛ ቆሮ. 6:1:: ከመካከላችሁ አንድ ሰው ከሌላው ጋር ሙግት ቢኖረው፣ ጉዳዩን በቅዱሳን ፊት በማቅረብ ፈንታ እንዴት ደፍሮ በማያምኑ ሰዎች ፊት ለመፋረድ ያቀርባል?

1ኛ ቆሮ. 6:4-6:: እንግዲህ እንዲህ ያለ ጉዳይ ሲያጋጥማችሁ፣ በቤተ ክርስቲያን የተናቁን ሰዎች ፈራጅ አድርጋችሁ ሹሙ! ይህንንም የምለው ላሳፍራችሁ ብዬ ነው:: ለመሆኑ ከመካከላችሁ ወንድሞችን ለማስታረቅ የሚበቃ አስተዋይ ሰው የለምን? ነገር ግን ወንድም ወንድሙን ለመክሰስ ፍርድ ቤት ይሄዳል፤ ያውም በማያምኑ ሰዎች ፊት!

25. ሌላውን ክርስቲያን ወደ ፍርድ ቤት ከመውሰድ ይልቅ ለመበደል ፍቀዱ::

1ኛ ቆሮ. 6:7:: እንግዲህ በመካከላችሁ መካሰስ መኖሩ ራሱ ውድቀታችሁን ያሳያል:: ብትበደሉስ አየሻልምን?

26. ጥላቻንና ጠብን የሚፈጥሩትን ባሕርያት አስወግዱ::



ኤፌ. 4:31:: መራርነትን ሁሉ፣ ቍጣና ንዴትን፣ ጭቅጭቅና ስድብን ከማንኛውም ክፋት ጋር ከእናንተ ዘንድ አስወግዱ::

27. የበደሏችሁን ሰዎች ይቅር በሉ:: እግዚአብሔር ይቅር እንዳላችሁ ይቅር በሉ:: ይህም፣ እግዚአብሔር እናንተን ይቅር ባለበት መንገድ መሆን አለበት:: ሌሎችን ይቅር በማለት እግዚአብሔርን ምሰሉ:: ከይቅርታ ውጪ ሰላምና እርቅ ፈጽሞ አይኖርም::

ኤፌ. 4:32:: እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተም ይቅር ተባባሉ፤ እርስ በርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ::

ኤፌ. 5:1-2:: እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን ምሰሉ፤ ክርስቶስ እንደ ወደደን ራሱንም ስለ እኛ መልካም መዐዛ ያለው መባና መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር እንደ ሰጠ እናንተም በፍቅር ተመላለሱ::

# ስደት

ማስታወሻ:- በስደት መሠቃየት አንተ እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር በመሆንህ ምክንያት በሌሎች በኩል የሚደርስብህ እንግልት ነው:: ይህም በሐሰት መከሰስን፣ ያለ ፍትሕ ፍርድ መቀበልን ወይም መታሠርን፣ መዘባበቻ መሆንን፣ መናቅን፣ ተቀባይነት ማጣትን ወይም መጐዳትን ያካትታል:: ስደት ክፉ በማድረጋችን ምክንያት ወይም ትክክለኛ ባለሥልጣናትን ባለመታዘዛችን ምክንያት የምንቀበለው መከራ አይደለም::

1. ለምንድን ነው ሰዎች፣ መልካም ቢያደርጉም እንኳን ክርስቲያኖችን የሚያሳድዷቸው?

ዮሐ. 15:18-21:: ዓለም ቢጠላችሁ፣ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ ዕወቁ:: ከዓለም ብትሆኑ ኖሮ፣ ዓለም የራሱ እንደ ሆኑት አድርጎ በወደዳችሁ ነበር፤ ከዓለም ለይቼ ስለ መረጥኋችሁ የዓለም አይደላችሁም፤ ዓለም የሚጠላችሁም ስለዚሁ ነው:: አገልጋይ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስታውሱ:: እኔን አሳደውኝ ከሆነ፣ እናንተንም ያሳድዷችኋል:: ቃሌን ጠብቀው ከሆነም ቃላችሁን ይጠብቃሉ:: የላከኝን ስለሚያውቁ፣ በስሜ ምክንያት ይህን ያደርጉባችኋል::

2ኛ ጢሞ. 3:10-14:: አንተ ግን ትምህርቴን፣ አካሄዴን፣ ዐላማዬን፣ እምነቴን፣ ትዕግሥቴን፣ ፍቅሬንና፣ ጽናቴን ሁሉ ታውቃለህ፤ ስደቴንና መከራዬን፣ በአንጾኪያና በኢቆንዮን፣ በልስጥራንም የደረሰብኝን ሁሉ፣ የታገሥሁትንም ስደት ታውቃለህ፤ ጌታ ግን ከእነዚህ ሁሉ አዳነኝ:: በእርግጥም በክርስቶስ ኢየሱስ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ:: ክፉዎችና አታላዮች ግን እየሳቱና እያሳቱ፣ በክፋትም ላይ ክፋትን እየጨመሩ ይሄዳሉ:: አንተ ግን በተማርኸውና በተረዳኸው ጽና፤ ይህን ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና::

1ኛ ዮሐ. 3:1:: የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠራ አብ አትረፍርፎ ያፈሰሰልን ፍቅር ምንኛ ታላቅ ነው! እኛም እንዲሁ ልጆቹ ነን:: ዓለም እኛን የማያውቀንም እርሱን ስላላወቀው ነው::



2. ቃየን የራሱ ሥራ ክፉ የወንድሙ የአቤል ሥራ ግን ጽድቅ መሆኑን ስላወቀ ወንድሙን አቤልን አሳደደው::

ዘፍ. 4:2-7::

1ኛ ዮሐ. 3:12-14:: የክፉው ወገን ሆኖ ወንድሙን እንደ ገደለው እንደ ቃየን አትሁኑ፤ ለምን ገደለው? ምክንያቱም የእርሱ ሥራ ክፉ፣ የወንድሙ ግን ጽድቅ ስለ ነበረ ነው:: ወንድሞች ሆይ፤ ዓለም ቢጠላችሁ አትደነቁ:: ወንድሞቻችንን ስለምንወድ ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፤ ፍቅር የሌለው ሁሉ በሞት ይኖራል::

3. ለሚያሳድዷችሁ ሰዎች መልካም አድርጉ፣ እንዲሁም ጸልዩላቸው:: ጠላቶቻችሁን ውደዱ::

ማቴ. 5:38-42:: <ዓይን ስለ ዓይን፣ ጥርስ ስለ ጥርስ> እንደ ተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ፤ <ክፉ አድራጊውን ሰው አትቃወሙት>፤ ነገር ግን ቀኝ ጉንጭህን ለሚመታህ ሌላውን ጉንጭህን ደግሞ አዙርለት:: አንድ ሰው እጀ ጠባብህን ሊወስድ ቢከስህ ካባህን ጨምረህ ስጠው:: አንድ ሰው አንድ ኪሎ ሜትር ተኩል የሚያህል ርቀት እንድትሄድ ቢያስገድድህ ዕጥፉን መንገድ አብረኸው ሂድ:: ለሚለምንህ ስጥ፤ ከአንተም ሊበደር የሚሻውን ፊት አትንሣው::»

ማቴ. 5:43-48::

ማቴ. 5:43-48:: «<ወዳጅህን ውደድ፤ ጠላትህን ጥላ> እንደ ተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ እላችኋለሁ:: እንደዚህም በማድረጋችሁ በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆናላችሁ፤ እርሱ ፀሐዩን ለክፉዎችና ለደጎች ያወጣል፤ ዝናቡንም ለኀጢአተኞችና ለጻድቃን ያዘንባል::

ሮሜ 12:14:: የሚያሳድዷችሁን መርቁ፤ መርቁ እንጂ አትርገሙ::

4. እየወገሩት ሳለ ስለ አሳዳጆቹ የጸለየውን እስጢፋኖስን ምሰሉ::

ሐዋ. 7፥60:: ከዚያም ተንበርክኮ፣ በታላቅ ድምፅ፣ «ጌታ ሆይ! ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው» ብሎ ጮኸ፤ ይህን ካለ በኋላም አንቀላፋ::

5. ከአሳዳጆቻችሁ ጋር ስትኖሩ ጠቢባንና የዋሆች ሁኑ::

ማቴ. 10፥16:: «እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ብልኆች እንደ ርግብ የዋሃን ሁኑ::»

6. በሐሰት ተከስሳችሁ እንደ ሆነ፣ እግዚአብሔር እንዲመራችሁ ታመኑት::

ማቴ. 10፥17-20:: ሰዎች ይዘው ለፍርድ ወደ ሸንጎ ያቀርቧችኋል፤ በምኵራቦቻቸውም ይገርፏችኋል፤ ስለዚህ ከእነርሱ ተጠንቀቁ:: በእኔ ምክንያት ወደ ገዦችና ወደ ነገሥታት ትወሰዳላችሁ፤ በእነርሱና በአሕዛብም ፊት ምስክር ትሆናላችሁ:: በምትያዙበትም ጊዜ ምን እንናገራለን፣ ምንስ እንመልሳለን ብላችሁ አትጨነቁ፤ በዚያን ጊዜ የምትናገሩት ይሰጣችኋል፤ በእናንተ የሚናገረው የሰማዩ አባታችሁ መንፈስ እንጂ እናንተ አይደላችሁምና::

7. ማንም ሰው አስከፊ ስለሆነው ስደት መጨነቅ የለበትም:: ስለዚያም ጳውሎስ ይመሰክራል::

2ኛ ቆሮ. 4፥8-9:: ከየአቅጣጫው ብንገፋም አንንኰታኰትም፤ ግራ ብንጋባም ተስፋ አንቈርጥም፤ ብንሰደድም ተጥለን አንቀርም፤ መትተው ቢጥሉንም አንጠፋም::

2ኛ ቆሮ. 11፥23-29:: *(ጳውሎስ በአሳዳጆቹ በኩል ስለ ተቀበለው ብዙ መከራ ይናገራል::)*

8. ስለ ክርስቶስ ሲሉ መከራን የሚቀበሉ ሰዎች ይባረካሉ፣ እንዲሁም ይህንኑ ጉዳይ እንደ ክብር መቁጠር አለባቸው::

1ኛ ጴጥ. 4፥12-16:: ወዳጆች ሆይ፤ እንደ እሳት የሚፈትን ብርቱ መከራ በመቀበላችሁ እንግዳ ነገር እንደ ደረሰባችሁ በመቍጠር አትደነቁ፤ ነገር ግን ክብሩ በሚገለጥበት ጊዜ ደስታችሁ ታላቅ እንዲሆን የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች በመሆናችሁ ደስ ይበላችሁ::



ስለ ክርስቶስ ስም ብትሰደቡ፣ የክብር መንፈስ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ስለሚያርፍ ብፁዓን ናችሁ:: ከእናንተ ማንም መከራን የሚቀበል ቢኖር፣ ነፍስ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ወንጀለኛ ወይም በሰው ነገር ጣልቃ ገቢ ሆኖ መከራን አይቀበል፤ ክርስቲያን በመሆኑ መከራ ቢደርስበት ግን ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር::

9. ከሚሰደዱ ጋር ለመተባበር አትፈሩ:: ይልቁንም፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ ከእነርሱ ጋር አብራችሁ መከራን ተቀበሉ::

2ኛ ጢሞ. 1፥8-9:: እንግዲህ፣ ስለ ጌታችን ለመመስከር ወይም የእርሱ እስረኛ በሆንሁት በእኔ አትፈር፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ኀይል ስለ ወንጌል ከእኔ ጋር መከራን ተቀበል፤ እኛ ስላደረግነው አንዳች ነገር ሳይሆን ከዕቅዱና ከጸጋው የተነሣ ያዳነን ወደ ቅዱስ ሕይወትም የጠራን እርሱ ነው:: ይህም ጸጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን::

10. በወንጌል አትፈሩ:: በድፍረት መስክሩ፤ መከራን ለመቀበልም ተዘጋጁ::

2ኛ ጢሞ. 2፥3:: እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ በጎ ወታደር፣ ከእኛ ጋር መከራን ተቀበል::

2ኛ ጢሞ. 2፥8-10:: ከሙታን የተነሣውን፣ ከዳዊት ዘርም የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስብ፤ የእኔም ወንጌል ይኸው ነው፤ ለዚህም እንደ ወንጀለኛ እስከ መታሰር ድረስ መከራን እየተቀበልሁ ነው፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን አይታሰርም:: ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን መዳን ከዘላለም ክብር ጋር እነርሱ ያገኙ ዘንድ፣ ለተመረጡት ስል ሁሉንም በመታገሥ እጸናለሁ::

11. አትናወጡ ወይም በስደት በኩል ሰይጣን ከእውነት መንገድ እንዲያርቃችሁ አትፍቀዱለት::

1ኛ ተሰ. 3፥2-4:: በእምነታችሁ እንዲያጸናችሁና እንዲያበረታችሁ ወንድማችንንና በክርስቶስ ወንጌል ሥራ ከእኛ ጋር የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነውን ጢሞቴዎስን ልከንላችኋል፤

ይኸውም በዚህ ፈተና ማንም እንዳይናወጥ ነው። እኛም ለዚህ ነገር እንደ ተመደብን እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ። በእርግጥ ከእናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ መከራ እንደሚደርስብን በየጊዜው እንነግራችሁ ነበር፤ እንደምታውቁትም እንዲሁ ደግሞ ሆኖአል።

12. ኢየሱስም አንዳንዶች በተሰደዱ ጊዜ እንደሚወድቁ ተናገረ። ማቴ. 13:1-9። (የዘሪው ምሳሌ)

ማቴ. 13:18-23። (ኢየሱስ ምሳሌዎቹን ተረጐመ።)

ማቴ. 13:20-21። «በድንጋያማ መሬት ላይ የተዘራው፣ ቃሉን ሰምቶ ወዲያውኑ በደስታ የሚቀበለውን ሰው ይመስላል። ነገር ግን ሥር መስደድ ባለመቻሉ ብዙ አይቈይም፤ በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት ሲመጣ ወዲያውኑ ይሰናከላል።»

13. አንዳንዶች ስደትን ለመሸሽ ሲሉ ወንጌልን አመቻምቸው ይሰብካሉ። እንደዚያ አትሁኑ።

ገላ. 6:12። ውጫዊ በሆነ ነገር ለመታየት የሚፈልጉ ሰዎች ትገረዙ ዘንድ ሊያስገድዷችሁ ይጥራሉ፤ ይህንም የሚያደርጉት ስለ ክርስቶስ መስቀል እንዳይሰደዱ ነው።

14. አማኞች ሲሰደዱ የእግዚአብሔርን ቃል ይጠብቃሉ። ዳዊትም አድርጎታል።

መዝ. 119:51። እብሪተኞች እጅግ ተሣለቁብኝ፤ እኔ ግን ከሕግህ ንቅንቅ አልልም።

መዝ. 119:61። የክፉዎች ገመድ ተተበተበብኝ፤ እኔ ግን ሕግህን አልረሳሁም።

መዝ. 119:69። እብሪተኞች ስሜን በሐሰት አጠፉ፤ እኔ ግን ትእዛዝህን በፍጹም ልብ እጠብቃለሁ።

15. አሳዳጆች ቢያስፈራሯችሁም እንኳን፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ እንዳደረጉት፣ ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን ታዘዙ።

ሐዋ. 4:18-20። ከጠሯቸውም በኋላ፣ በኢየሱስ ስም ፈጽሞ እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዟቸው። ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን



መልሰው እንዲህ አሏቸው፤ «ከእግዚአብሔር ይልቅ ለእናንተ መታዘዝ በእግዚአብሔር ፊት ይገባ እንደሆነ እስቲ እናንተው ፍረዱ፤ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ወደ ኋላ አንልም።»

ሐዋ. 5:17-32። (ሐዋርያት ወንጌል መስበኩን ቀጠሉ።)

ሐዋ. 5:29። ጴጥሮስና ሌሎች ሐዋርያትም መልሰው እንዲህ አሉ፤ «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል!»

ሐዋ. 5:41-42። ሐዋርያትም፣ ስለ ስሙ ውርደትን ለመቀበል በመብቃታቸው ደስ እያላቸው ከሸንጎው ወጥተው ሄዱ፤ በየዕለቱም፣ በቤተ መቅደስም ሆነ በየቤቱ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ከማስተማርና ከመስበክ ከቶ ወደ ኋላ አላሉም ነበር።

16. ጳውሎስና ሲላስ ታሥረው ሳሉ ማኅሌትን ለእግዚአብሔር ዘመሩ።

ሐዋ. 16:25። እኩለ ሌሊት አካባቢ ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩና እየዘመሩ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ነበር፤ ሌሎች እስረኞችም ያዳምጧቸው ነበር።

17. ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ሲል ለመሞት ፈቃደኛ ነበር።

ሐዋ. 21:12-13። ይህን ስንሰማ እኛና በዚያም የሚኖሩት ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ ለመነው። ጳውሎስ ግን፣ «ለምን እንዲህ እያለቀሳችሁ ልቤን ታባቡታላችሁ? እኔ መታሰር ቀርቶ ስለ ጌታ ኢየሱስ ስም በኢየሩሳሌም ለመሞት እንኳን ዝግጁ ነኝ» አላቸው።

18. ስለ ጽድቅ ሲሉ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው።

ማቴ. 5:10-12። ስለ ጽድቅ ብለው የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና። ሰዎች በእኔ ምክንያት ቢሰድቧችሁ፣ ቢያሳድዷችሁና ክፉውን ሁሉ በሐሰት ቢያስወሩባችሁ፤ ብፁዓን ናችሁ። በሰማይ የምትቀበሉት ዋጋ ታላቅ ስለ ሆነ ደስ ይበላችሁ፤ ሐሤት አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያት እንዲሁ አሳደዋቸዋልና።

2ኛ ጢሞ. 4:6-8። እኔ እንደ መጠጥ ቍርባን መሥዋዕት

ለመፍሰስ ተቃርቤአለሁ፤ ተለይቼ የምሄድበት ጊዜ ደርሶአል:: መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፤ ሩጫውን ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖትንም ጠብቂአለሁ:: ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ በዚያ ቀን ለእኔ ይሰጠኛል፤ ደግሞም ለእኔ ብቻ ሳይሆን፣ የእርሱን መገለጥ ለናፈቁ ሁሉ ነው::

ራእይ 2:9-10:: መከራህንና ድኽነትህን ዐውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ ሀብታም ነህ፤ አይሁድ ሳይሆኑ አይሁድ ነን እያሉ ስምህን የሚያጠፉትን ዐውቃለሁ፤ እነርሱ ግን የሰይጣን ማኅበር ናቸው:: ሊደርስብህ ያለውን መከራ አትፍራ:: እነሆ፤ ዲያብሎስ ሊፈትናችሁ አንዳንዶቻችሁን ወደ እስር ቤት ይጥላል፤ ዐሥር ቀንም መከራ ትቀበላላችሁ:: እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ሁን፤ እኔም የሕይወትን አክሊል እሰጥሃለሁ::

19. ዕብራውያን ክርስቲያኖች መሠረታቸውን ከስደት በታች አድርገው ቆሙ:: ስለዚህም ተሸለሙ::

ዕብ. 10:32-39::

ዕብ. 10:33-35:: አንዳንድ ጊዜ በአደባባይ ለስድብና ለስደት ተጋልጣችሁ ነበር፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ እንደዚህ ያለ መከራ ከደረሰባቸው ሰዎች ጋር አብራችሁ መከራን ተቀብላችኋል:: እናንተ ራሳችሁ የተሻለና ለዘወትር የሚኖር ሀብት ያላችሁ መሆናችሁን ስለምታውቁ ለታሰሩት ራራችሁ፤ ንብረታችሁም ሲዘረፍ በደስታ ተቀበላችሁ:: ስለዚህ ታላቅ ዋጋ ያለውን መታመናችሁን አትጣሉ::

20. መልካም በማድረጋችሁ ምክንያትም ቢሆን መከራን ለመቀበል ፈቃደኞች ሁኑ::

1ኛ ጴጥ. 3:13-22::

1ኛ ጴጥ. 3:13-14:: መልካም ነገር ለማድረግ ብትቀኑ የሚጐዳችሁ ማን ነው? ነገር ግን ስለ ጽድቅ እንኳ መከራ ቢደርስባችሁ ብፁዓን ናችሁ፤ «ዛቻቸውን አትፍሩ፤ አትታወኩም::»

1ኛ ጴጥ. 3:17:: የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲህ ከሆነ፣ ክፉ ሠርቶ መከራ ከመቀበል ይልቅ መልካም አድርጎ መከራ መቀበል ይሻላል::



21. ያልተለወጡ ኀጢአተኞች ከእነርሱ ጋር ባለመተባበራችሁ ምክንያት ጭቆናን ሊጭኑባችሁ ይችላሉ::

1ኛ ጴጥ. 4:3-5:: አሕዛብ ፈቅደው እንደሚያደርጉት በመዳራት፣ በሥጋዊ ምኞት፣ በስካር፣ በጭፈራ፣ ያለ ልክ በመጠጣት፣ በአስጸያፊ የጣዖት አምልኮ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃል:: ይህን በመሰለ ብኩን ሕይወት ከእነርሱ ጋር ስለ-ማትሮጡ እንግዳ ሆኖባቸው በመደነቅ ይሰድቧችኋል::

22. በጸጋና በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የዳንን እኛ ስለ እርሱ መከራን ለመቀበል መፍቀድና መዘጋጀት አለብን::

ፊል. 1:27-30::

ፊል. 1:29-30:: በክርስቶስ እንድታምኑ ብቻ ሳይሆን ስለ እርሱ መከራ እንድትቀበሉም ይህ ጸጋ ተሰጥቶአችኋልና፤ ቀድሞ እንዳያችሁት አሁንም በእኔ እንዳለ በምትሰሙት በዚያው ዐይነት ተጋድሎ እናንተም እያለፋችሁ ነውና::

23. ስትሰደዱ በምን ዓይነት መንገድ ምላሽ መስጠት አለባችሁ? ጳውሎስ እንዴት አድርጎ ይህንን ጉዳይ እንደያዘው እስቲ ተመልከቱ::

1ኛ ቆሮ. 4:9-13::

1ኛ ቆሮ. 4:11-13:: እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፤ እንጠማለን፤ እንራቈታለን፤ እንደበደባለን፤ ያለመጠለያ እንንከራተታለን፤ በገዛ እጃችን እየሠራን እንደክማለን:: ሲረግሙን እንመርቃለን፤ ሲያሳድዱን እንታገሣለን፤ ስማችንን ሲያጠፉ መልካም እንመልሳለን:: እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጉድፍ፣ የምድር ጥራጊ ሆነናል::

# ጸሎት፣ እግዚአብሔርን መጠበቅ

በተጨማሪ መታመንን በገጽ 224 ላይ ተመልከት።

**1. የጌታ ጸሎት የእኛ ምሳሌ ነው።**

*ማቴ.* 6:9-13።

**2. «አባታችን ሆይ»ን ጸልዩ።**

*ማቴ.* 6:9። እናንተ ግን እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ፤ «በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤ ስምህ ይቀደስ።»

**3. ለዕለት ተዕለት ፍላጐቶቻችሁ ጸልዩ።**

*ማቴ.* 6:11። የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን።

**4. በየዕለቱ ለኀጢአት ይቅርታ ጸልዩ።**

*ማቴ.* 6:12። እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል፤ በደላችንን ይቅር በለን።

**5. ፍላጐቶቻችንን ሁሉ በሚረዳው ሊቀ ካህናችን በኢየሱስ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር በድፍረት መቅረብ እንችላለን።**

*ዕብ.* 4:14-16። እንግዲህ ወደ ሰማያት ያረገ ታላቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፣ እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ። በድካማችን የማይራራልን ሊቀ ካህናት የለንምና፤ ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን፤ ይሁን እንጂ ምንም ኀጢአት አልሠራም። እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበልና በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ፣ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።

**6. የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በጌታ ላይ ጣሉት።**

1ኛ ጴጥ. 5:6-7። ስለዚህ እርሱ በወሰነው ጊዜ ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፤ እርሱ ስለ እናንተ ስለሚያስብ የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።

**7. ከመስጋት ይልቅ ስለማናቸውም ነገሮች ጸልዩ።**



*ፊል.* 4:6-7። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ፣ ከምስጋናም ጋር ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ እንጂ ስለ ማንኛውም ነገር አትጨነቁ። ከማስተዋል ሁሉ በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሰላም፣ ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።

**8. ሳታቋርጡ ጸልዩ፣ እንዲሁም በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ አመስግኑ።**

1ኛ ተሰ. 5:17-18። ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በማናቸውም ሁኔታ አመስግኑ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእናንተ ይህ ነውና።

**9. በእምነት ጸልዩ።**

*ያዕ.* 1:6። ዳሩ ግን ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ ምክንያቱም የሚጠራጠር ሰው በነፋስ እንደሚገፋና እንደሚናወጥ የባሕር ማዕበል ነው።

**10. በሕመም ጊዜ ጸልዩ።**

*ያዕ.* 5:14-16።

**11. የጻድቅ ሰው ጸሎት ኀይለኛ ነው።**

*ያዕ.* 5:16። ስለዚህ ኀጢአታችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ፤ ትፈወሱም ዘንድ አንዱ ለሌላው ይጸልይ። የጻድቅ ሰው ጸሎት ኀይል አለው፤ ታላቅ ነገርም ያደርጋል።

**12. ኤልያስ እንዳደረገው፣ ለታላላቅ ነገሮች ለመጸለይ ድፈሩ።**

*ያዕ.* 5:17-18። ኤልያስ እንደ እኛ ሰው ነበረ፤ ዝናብ እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፤ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ተኩል ዝናብ አልዘነበም። እንደ ገናም ጸለየ፤ ዝናብም ከሰማይ ዘነበ፤ ምድርም ፍሬዋን ሰጠች።

**13. እግዚአብሔር ጸሎትን ይሰማል፣ ይመልስማል፤ እርሱ ለልጆቹ ቅርብ ነው።**

*መዝ.* 34:15-18። የእግዚአብሔር ዐይኖች ወደ ጻድቃን ናቸው ጆሮዎቹም ለጩኸታቸው ክፍት ናቸው። መታሰቢያቸውን ከምድር

ለማጥፋት፣ የእግዚአብሔር ፊት በክፉ አድራጊዎች ላይ ነው። ጻድቃን ሲጮኹ፣ እግዚአብሔር ይሰማቸዋል፤ ከመከራቸውም ሁሉ ያድናቸዋል። እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፤ መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል።

**14. ጸልዩና ባገኛችሁት መንገድ ሁሉ ሥሩ።**

ነህ. 4:9። እኛ ግን ወደ እግዚአብሔር ጸለይን፤ ዛቻቸውንም ለመቋቋም ቀንና ሌሊት የሚጠብቁ ዘቦችን መደብን።

**15. በመንገዳችሁ ሁሉ ጌታን እወቁ።**

ምሳ. 3:5-6። በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን ዕወቅ፤ እርሱም ጐዳናህን ቀና ያደርገዋል።

**16. ጌታችሁን በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት።**

ኢሳ. 55:6። እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፤ ቀርቦም ሳለ ጥሩት።

**17. ስለ ጸጋውና ምሕረቱ እግዚአብሔርን አመስግኑት፣ አወድሱት፣ ምሕረቱንም መፈለጋችሁን ቀጥሉ።**

መዝ. 105:1-4።

**18. ለተመለሰ ጸሎት እግዚአብሔርን አመስግኑት፣ አወድሱት።**

መዝ. 66:13-20።

መዝ. 66:17-20። በአፌ ወደ እርሱ ጮኽሁ፤ በአንደበቴም አመሰገንሁት። ኀጢአትን በልቤ አስተናግጄ ቢሆን ኖሮ፣ ጌታ ባልሰማኝ ነበር። አሁን ግን እግዚአብሔር በእርግጥ ሰምቶኛል፤ ጸሎቴንም አድምጦአል። ጸሎቴን ያልናቀ፣ ምሕረቱንም ከእኔ ያላራቀ፣ እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው።

**19. ለኀጢአት ይቅርታ ጸልዩ።**

መዝ. 32 እና 51።

ኤር. 29:12-13። እናንተም ትጠሩኛላችሁ፤ ቀርባችሁ ወደ እኔ ትጸልያላችሁ፤ እኔም እሰማችኋለሁ። እናንተ ትፈልጉኛላችሁ፣



በፍጹም ልባችሁም ከፈለጋችሁኝ ታገኙኛላችሁ።

ማቴ. 11:28-30። እናንት ሸክም የከበዳችሁና የደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም ዕረፍት እሰጣችኋለሁ። ቀንበሬን ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ በልቤ የዋህና ትሑት ነኝና፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና።

ሮሜ 10:13። «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።»

1ኛ ዮሐ. 1:7-9።

በተጨማሪም የኃጢአቶች ይቅርታን በገጽ 90 ይመልከቱ።

**20. በመከራ ጊዜ ጌታን ጥራ።**

መዝ. 50:15። በመከራ ቀን ጥራኝ፤ አድንሃለሁ፤ አንተም ታከብረኛለህ።

**21. ኢየሱስ ልክ እንደ እኛ የተፈተነ ስለሆነ፣ ሊረዳን ይችላል።**

ዕብ. 2:18። እርሱ ራሱ በተፈተነ ጊዜ መከራን ስለ ተቀበለ፣ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።

ዕብ. 3:1። እንግዲህ የሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፤ የእምነታችን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት የሆነውን ኢየሱስን አስቡ።

**22. እግዚአብሔር የምልጃ ጸሎትን ይመልሳል።**

ሐዋ. 12:1-17። «ጴጥሮስ ያለፍትሕ ታስሮ ነበር። ቤተ ክርስቲያን ለጸሎት ተሰበሰበች። ጴጥሮስ ወዲያውኑ ተፈታ።»

ሐዋ. 12:5። ጴጥሮስ በዚህ መሠረት እስር ቤት ተጣለ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ግን ስለ እርሱ አጥብቃ ወደ እግዚአብሔር ትጸልይ ነበር።

ሐዋ. 12:12። ይህን ከተረዳ በኋላም፣ ብዙ ሰዎች ተሰብስበው በአንድነት ወደሚጸልዩበት፣ ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት ሄደ።

# እድገታዊ ቅድስና

## (በእምነትና በመንፈሳዊነት ማደግ)

በተጨማሪ ኃጢአትን ድል መንሣት የሚለውን በገጽ 142 ተመልከቱ::

1. በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ::

2ኛ ጴጥ. 3:18:: ነገር ግን በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ዕውቀት እደጉ፤ ለእርሱ አሁንም፣ ለዘላለምም ክብር ይሁን፤ አሜን::

2. እንደ ብዙዎቹ ዕብራውያን፣ ያልበሰልክ ክርስቲያን ሆነህ እንደ ሆነ በዚያ አትርካ::

ዕብ. 5:11-6:4::

ዕብ. 5:12-14:: በዚህ ጊዜ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፣ ገና የእግዚአብሔርን ቃል የመጀመሪያ ትምህርት የሚያስተምራችሁ ሰው ያስፈልጋችኋል፤ የሚያስፈልጋችሁም ጠንካራ ምግብ ሳይሆን ወተት ነው:: ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለሆነ፣ ከጽድቅ ትምህርት ጋር ገና አልተዋወቀም:: ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙን ከክፉው ለመለየት ራሳቸውን ላስለመዱ፣ ለበሰሉ ሰዎች ነው::

3. እግዚአብሔር እኛን ወደ መንፈሳዊ ብስለትና ቅድስና ለማምጣት በቃሉ አማካይነት በውስጣችን ይሠራል::

ዮሐ. 17:17:: (ኢየሱስ ስለተቤዣቸው ሕዝቡ እያሰበ ጸለየ::) ቃልህ እውነት ነው፤ በእውነትህ ቀድሳቸው::

ቈላ. 3:16:: የክርስቶስ ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ እርስ በርሳችሁ በጥበብ ሁሉ ተማማሩ፤ ተመካከሩ፤ በመዝሙርና በማሕሌት፣ በመንፈሳዊም ቅኔ በማመስገን በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ::

1ኛ ጴጥ. 2:2-3:: በድነታችሁ እንድታድጉ፣ አዲስ እንደ ተወለዱ ሕፃናት ንጹሑን መንፈሳዊ ወተት ተመኙ፤ ጌታ መልካም መሆኑን ቀምሳችኋልና::

መዝ. 119:11:: አንተን እንዳልበድል፤ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ::



መዝ. 119:105:: ሕግህ ለእግሬ መብራት፣ ለመንገዴም ብርሃን ነው::

4. እስትንፋስ እግዚአብሔርን የያዘውና ከስሕተት የጸዳው መጽሐፍ ቅዱስ፣ እኛ ለበጐ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀን እንድንሆን እግዚአብሔር በጽድቅ ሲያሠለጥነን የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው::

2ኛ ጢሞ. 3:16-17:: ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው::

5. መካሪው፣ መንፈስ ቅዱስ፣ በራሱ ቃል በኩል ያስተምረናል::

ዮሐ. 14:25-26:: «አሁን ከእናንተ ጋር እያለሁ ይህን ሁሉ ነግሬአችኋለሁ፤ አብ በስሜ የሚልከው አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል::»

6. የእግዚአብሔር ቃል ከልክ በላይ ውጤታማ ነው::

ዕብ. 4:12:: የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ ነውና፤ በሁለት በኩል ስለት ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ ስለታም ነው፤ ነፍስንና መንፈስን፣ ጅማትንና ቅልጥምን እስኪለያይ ድረስ ዘልቆ ይወጋል፤ የልብንም ሐሳብና ምኞት ይመረምራል::

7. ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳደረገው፣ በሩጫ ላይ እንዳለ ሯጭ ድልን እስከምታገኙ ድረስ ትግሉን ቀጥሉ::

ፊል. 3:12-14:: ይህን ሁሉ አግኝቻለሁ ወይም ፍጹም ሆኛለሁ ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ክርስቶስ ኢየሱስ እኔን የራሱ ያደረገበትን ያን፣ እኔም የራሴ ለማድረግ እጣጣራለሁ:: ወንድሞች ሆይ፤ እኔ እንደ ያዝሁት አድርጌ ራሴን አልቈጥርም፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ ከኋላዬ ያለውን እየረሳሁ ከፊቴ ወዳለው እዘረጋለሁ:: እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ላይ ስለ ጠራኝ፣ ሽልማት ለመቀዳጀት ወደ ግቡ እፈጥናለሁ::

ማስታወሻ፡- ጳውሎስ በሳል ክርስቲያን ቢሆንም እንኳ፣ ስለ ራሱ ጤነኛ የሆነ ያለመርካት ስሜት ነበረው:: ባለፈው ስሕተቱ ላይ አያተኩርም ነበር፣ ወይም ከወደቀ በኋላ በውድቀቱ ተስፋ ቆርጦ ለመቀመጥ ፈቃደኛ አልነበረም:: ወደ ፊት ገፋ (ትግሉን ቀጠለ)::

**8. ሩጫውን በጽናት እንዳትሮጥ የሚያደርጉህን እንቅፋቶች ሁሉ አስወግድ::**

ዕብ. 12:1:: እንግዲህ እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፣ ሸክም የሚሆንብንን ሁሉ፣ በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኀጢአት አስወግደን በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ::

**9. የእምነታችሁ ጀማሪና ፈጻሚ በሆነው በኢየሱስ ላይ አተኩሩ:: እናንተን ለማዳን ባደረገው ነገር ሁሉ ላይ ትኩረት አድርጉ::**

ዕብ. 12:2:: የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንመልከት፤ እርሱ በፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉን ታግሦ፣ የመስቀሉንም ውርደት ንቆ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአል::

**10. መንፈሳዊ ለመሆን ራስህን አስለምድ:: ሁልጊዜ በልምምዱ እንደሚገፋ አትሌት (ስፖርተኛ) ሁን:: ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የመከረው ያን እንዲያደርግ ነው::**

1ኛ ጢሞ. 4:7-8:: እግዚአብሔርን ከማያከብር ርባና ቢስ አፈ ታሪክና ከአሮጊቶች ተረታ ተረት ራቅ፤ ይልቁንም ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ራስህን አሠልጥን:: የአካል ብቃት ልምምድ ለጥቂት ነገር ይጠቅማልና፤ ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ራስን ማሠልጠን ግን ለአሁኑም ሆነ ለሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው ለሁለቱም ይጠቅማል::

**11. መንፈሳዊ ሕይወትን ለመኖር ብርቱ ጥረት አድርግ::**

2ኛ ጴጥ. 3:14:: ስለዚህ ወዳጆች ሆይ፤ እነዚህን ሁሉ ነገሮች የምትጠባበቁ ስለ ሆናችሁ፣ ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ ከእርሱ ጋር በሰላም እንድትገኙ ትጉ::



**12. እግዚአብሔርን ለማክበር፣ በእርሱ ብቻ ብዙ ፍሬ ልታፈሩ በምትችሉበት በወይኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ኑሩ::**

ዮሐ. 15:1-8::

ዮሐ. 15:1:: «እውነተኛው የወይን ተክል እኔ ነኝ፤ አትክልተኛውም አባቴ ነው::»

ዮሐ. 15:5:: «እኔ የወይን ተክል ነኝ፤ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ:: ማንም በእኔ ቢኖር እኔም በእርሱ ብኖር፣ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል፤ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና::»

ዮሐ. 15:8:: «ብዙ ፍሬ በማፍራት ደቀ መዛሙርቴ መሆናችሁን ብትገልጡ፣ በዚህ አባቴ ይከብራል::»

**13. ክርስቶስን በይበልጥ እንድትመስሉ የኢየሱስን ፈለግ ተከተሉ::**

1ኛ ዮሐ. 2:6:: ማንም በእርሱ እኖራለሁ የሚል፣ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል::

ይህን በበለጠ ለመረዳት ኢየሱስን መምሰል የሚለውን በገጽ 114 ላይ ተመልከት::

**14. ሐዋርያው ጴጥሮስ ኢየሱስን ልንመስልባቸው የምንችልባቸውን አንዳድ ባሕርያት ዘርዝሮልናል::**

2ኛ ጴጥ. 1:5-9::

2ኛ ጴጥ. 1:5-7:: በዚህም ምክንያት በሙሉ ትጋት በእምነታችሁ ላይ በጎነትን ለመጨመር ጣሩ፤ በበጎነት ላይ ዕውቀትን፣ በዕውቀት ላይ ራስን መግዛት፣ ራስን በመግዛት ላይ መጽናትን፣ በመጽናትም ላይ እውነተኛ መንፈሳዊነትን፤ በእውነተኛ መንፈሳዊነት ላይ ወንድማዊ መተሳሰብን፣ በወንድማዊ መተሳሰብ ላይ ፍቅርን ጨምሩ::

**15. በኢየሱስ ክርስቶስ መከራ፣ ሞትና ትንሣዔ የተነሣ ባገኘነው ድል አማካይነት በእምነትና በመንፈሳዊነት ለማደግ ልንሠራ መነቃቃት አለብን::**

1ኛ ቆሮ. 15:57-58:: ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ

በኩል ድልን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ጸንታችሁ ቁሙ፣ በምንም ነገር አትናወጡ። ለጌታ ሥራ ዘወትር የምትተጉ ሁኑ፤ ምክንያቱም ለጌታ የምትደክሙት በከንቱ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ።

2ኛ ቆሮ. 7:1። እንግዲህ፣ ወዳጆች ሆይ፤ ይህ የተስፋ ቃል ስላለን፣ ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን እናንጻ፤ እግዚአብሔርንም በመፍራት ቅድስናችንን ፍጹም እናድርገው።

ሮሜ 12:1-2። እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁ ነው። መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።

16. እግዚአብሔር፣ ነፍስን ይቀሰቅስ ዘንድ፣ አላዋቂዎችን አስተዋይ ያደርግ ዘንድ፣ ለልብ ደስታን ለመስጠት፣ ለዐይን ብርሃንን ለመስጠትና ከዚያም ላለፉ በርካታ ጉዳዮች፣ ቃሉን ይጠቀማል።

*መዝ. 19:7-11።*

*መዝ. 19:7-8።* የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስንም መልሶ ያለመልማል፤ የእግዚአብሔር ሥርዐት የታመነ ነው፤ አላዋቂውን ጥበበኛ ያደርጋል። የእግዚአብሔር ሕግጋት ትክክል ናቸው፤ ልብን ደስ ያሰኛሉ። የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፤ ዐይንን ያበራል።

17. እግዚአብሔር በቃሉና በመንፈሱ አማካይነት በውስጣችን ስለሚሠራ በሁሉም አቅጣጫ ደኅንነታችንን እንድንሠራው ይጠብቅብናል።

ፊል. 2:12-13፡ ስለዚህ፣ ወዳጆቼ ሆይ፤ ሁልጊዜም ታዛዦች እንደ ነበራችሁ ሁሉ፣ አሁንም እኔ በአጠገባችሁ ሳለሁ ብቻ ሳይሆን፣



ይልቁንም አሁን በሌለሁበት ጊዜ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ እንደ በጎ ፈቃዱ መፈለግንና ማድረግን በእናንተ ውስጥ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።

18. እግዚአብሔር በጸጋው ክርስቲያኖችን ሁሉ ይበልጥ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ መምሰል እንዲመጡ ይለውጣቸዋል።

2ኛ ቆሮ. 3:18። እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያንጸባረቅን፣ የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፤ ይህም የሚሆነው መንፈስ ከሆነ ጌታ ነው።